# የልጆች አስተዳደግ

ይህ የልጆች አስተዳደግ የተባለው መጽሐፍ ከአራቱ ተከታታይ መጻሕፍት ሦስተኛው ሲሆን አጠቃላይ ርዕሳቸው የተባረከ ቤተሰብ ተብለው ተሰይመዋል። የመጽሐፎቹም ስም በዝርዝር፡-

1ኛ የጋብቻ ዝግጅት

2ኛ የመተባበር ኑሮ

3ኛ የልጆች አስተዳደግ

4ኛ በተለይ ለወጣቶች

አዲስ አበባ

ማውጫ ገጽ


## ክፍል 1 - ልጆቻችሁ የክርስቶስ ተከታዮች እንዲሆኑ ማሠልጠን

ትምህርት 1 - ልጆችን ገና ከሕፃንነታቸው ጀምሮ የማሠልጠን ጥቅም . . . . . 1

ትምህርት 2 - ለልጆቻችሁ ማስተማር ያለባችሁ ነገሮች . . . . . . . . . 5

ትምህርት 3 - ልጆቻችሁን እንዴት እንደምታስተምሩ . . . . . . . . 8

## ክፍል 2 - ልጆችን የዘወትር ልማድ እንዲኖራቸው ማሠልጠን

ትምህርት 4 - ጸሎት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 11

ትምህርት 5 - በግል ከእግዚአብሔር ጋር የመሆኛ ጊዜ . . . . . . . . . 15

ትምህርት 6 - በቤተ ክርስቲያን የአምልኮ ጊዜ አዘውትሮ
የመገኘትና የመጋቢነት ልማድ . . . . . . . . . . . 19

## ክፍል 3 - ልጆች መልካም ጸባይ እንዲኖራቸው ማሠልጠን

ትምህርት 7 - ሥነ ሥርዓት . . . . . . . . . . . . . . . . . 23

ትምህርት 8 - መታዘዝን ለማስተማር የሚያገለግሉ መመሪያዎች . . . . . . 27

ትምህርት 9 - ልጆች እንዲታዘዙ ማድረግ . . . . . . . . . . . . 31

ትምህርት 10 - እግዚአብሔርንና ሰውን ማክበር . . . . . . . . . . 35

ትምህርት 11 - እውነተኛነትና ታማኝነት . . . . . . . . . . . . 39


ትምህርት 12 - ቸርነትና ርኅሩኅነት . . . . . . . . . . . . . . 42

ትምህርት 13 - ኃላፊነት . . . . . . . . . . . . . . . . . 45

## መግቢያ

ይህች ትንሽ መጽሐፍ እግዚአብሔር የሰጣችሁን ልጆች እንዴት እንደምታሳድጉ እንድትረዳችሁ በጸሎት ተዘጋጅታለች። በአእምሮአችሁ ውስጥ በእግዚአብሔር ቃል ላይ የተመሠረቱ ዓላማዎች ቢኖሩአችሁ፥ በየዕለቱ ለሚገጥሙአችሁ ሁኔታዎች መመሪያ ትሆናችኋለች። ስለነዚህም ዓላማዎች በእግዚአብሔር ላይ በመተማመን በያዕ. 1፡5 በተጠቀሰው የተስፋ ቃል መሠረት ጥበብን እንዲሰጣችሁ ጸልዩ። ቃሉም እንዲህ ይላል «ከእናንተ ግን ማንም ጥበብ ቢጎድለው በልግስና ለሁሉ የሚሰጠውን እግዚአብሔርን ይለምን፥ እርሱም ይሰጠዋል።»

በዚህ ጊዜ የምናስበው በተለይ ከሕፃናት አንሥቶ እስከ አሥራ ሁለት ወይም አሥራ ሦስት ዓመት ዕድሜ ያላቸውን ልጆች ነው። ልጆችን ማሳደግ ደረጃን በመውጣት ሊመሰል ይችላል። አንድን ደረጃ በአንድ ጊዜ ለመውጣት መሞከር በጣም ጥሩ ነው። ከሕፃንነት እስከ ብስለት አንድ ሕፃን የሚያልፋቸውን የዕድገት ደረጃዎች ከዚህ በታች በተመለከተው ሁኔታ ማቅረብ ይቻላል።




የመጀመሪያው ደረጃ ለልጃችሁ መታዘዝን ማስተማር ነው። የሚቀጥሉት ደረጃዎች በመጀመሪያውና ጠቃሚ በሆነው በመታዘዝ ላይ የተመሠረቱ ናቸው። ልጃችሁ እያደገ በሚሄድበት ጊዜ የመጀመሪያውን ደረጃ መታዘዝን ካስተማራችሁት በኋላ፥ የተቀሩትን ደረጃዎች በሙሉ በረዥም ጊዜ ውስጥ እያስተማራችሁት መምራት ትችላላችሁ። የዚህ ሁሉ ዋናው ዓላማ ልጃችሁን በነዚህ የዕድገት ደረጃዎች በመምራት የበሰለ ወጣት ሆኖ ጌታን የሚያውቅና የሚወድ እርሱንም ለማገልገል ፍላጎት ያለው እንዲሆን ነው።

# ክፍል 1

## ትምህርት 1-3

## ልጆቻችሁ የክርስቶስ ተከታዮች እንዲሆኑ ማሰልጠን

የክፍሉ ዓላማ:- ወላጆች ልጆቻቸውን ከሕፃንነታቸው አንስቶ ሊረዱአቸው በሚችሉት መንገድ የእግዚአብሔርን ቃል እያስተማሩ እንዲያሳድጉአቸው ማበረታታት።

የክፍሉ ጥቅስ:- «ልጅን በሚሄድበት መንገድ ምራው፤ በሸመገለም ጊዜ ከእርሱ ፈቀቅ አይልም።» ምሳ. 22:6

## ክፍል 1 - ትምህርት 1

## ልጆችን ገና ከሕፃንነታቸው ጀምሮ የማሠልጠን ጥቅም

የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል:- የሐዋ. ሥራ 16:1-3፤ 2ኛ ጢሞ. 1:3-8፤ 2ኛ ጢሞ. 3:14-15

ዓላማ:- ወላጆች ልጆቻቸው ገና ሕፃናት ሳሉ ማስተማር እንዲጀምሩ ለማበረታታት።

በቃል የሚጠና ጥቅስ:- «ከሕፃንነትህ ጀምረህ ክርስቶስ ኢየሱስን በማመን፥ መዳን የሚገኝበትን ጥበብ ሊሰጡህ የሚችሉትን ቅዱሳን መጻሕፍትን አውቀሃል።» 2ኛ ጢሞ. 3:15።

መግቢያ:- የሸክላ ሥራ ከጥንታዊው የሰው ልጅ ጥበብ አንዱ ነው። ክርስቶስ ወደዚህ ምድር ከመምጣቱ ከ5000 ዓመታት በፊት የተሠሩ የሸክላ ስብርባሪዎች ተገኝተዋል። በአንዳንድ ሀገሮች ሸክላ የሚሠሩት ወንዶች ናቸው። በሌሎች ሀገሮች ደግሞ የዚህ ሥራ ችሎታ ያላቸው ሴቶች ናቸው።

የሸክላ ሥራ ታላቅ ችሎታን ይጠይቃል። ትክክለኛ የሆነውን የጭቃ ዓይነት መገኘት አለበት። ከአፈሩ ውስጥ አንኳሩና ሥራ ሥሩ ተለቅመው ይወጣሉ። ከዚያ በኋላ ውኃ ይጨመርበትና እስኪለዝብ ድረስ ይቦካል።

ሸክላ ሠሪው ጭቃውን እንዳስፈለገው ድስት፥ እንስራ ወይም ጀበና አድርጎ ይሠራዋል። ትልቅና ጠፍጣፋ ምጣድ አድርጎ ሊሠራው ይችላል። ጭቃውን እንደዚህ እንደፈለገ አድርጎ ሊሠራው የሚችለው ለስላሳና እንደፈለገው አድርጎ እንዲሠራው የሚታዘዝለት ስለሆነ ነው።

ኤርምያስ 18:4 በብሉይ ኪዳን ጊዜ ስለነበረ ስለ አንድ ሸክላ ሠሪ ይነግረናል። ጥቅሱ «ከጭቃ ይሠራው የነበረ ዕቃ በሸክላ ሠሪው እጅ ተበላሸ፤ ሸክላ ሠሪውም እንደ ወደደ መልሶ ሌላ ዕቃ አድርጎ ሠራው» ይላል። የተበላሸውን ማሰሮ በእሳት ተለብልቦ ከመጠንከሩ በፊት እንደገና መልሶ መሥራት ይቻላል። ተመልሶ ጠቃሚ ዕቃ ተደርጎ ሊሠራ በሚችልበት ሁኔታ ላይ ነው ያለው። እግዚአብሔር ክርስቲያን ለሆኑ ወላጆቹ አእምሮአቸውና ልባቸው ለስላሳ የሆን

ልጆችን ሰጥቶአቸዋል። እነርሱን ጠቃሚ የሆነ ሕይወት እንዲኖራቸው አድርጎ ማሠልጠን ከእግዚአብሔር የተሰጣቸው ሥራ ነው።

## ገና ከሕፃንነታቸው ማስተማር ጀምሩ።

አንድ ሰው «በሕይወቱ መጀመሪያው ላይ የተማረው ነገር ለረዥም ጊዜ ይታወሰዋል» ሲል ተናግሯል። በልጅነታችሁ ስለ ሆኑት ነገሮች አሁንም ገና በአእምሮአችሁ የምታስታውሷቸውን ልታስቡ ትችላላችሁ? ትንሽ ልጅ ሳላችሁ ትኖሩበት የነበረውን ቤት ልታስታውሱ ትችላላችሁ? እነዚህ ትዝታዎች የማይዘነጉ ናቸው፥ አይደሉምን?

የሕፃን አእምሮ ክፍትና ለመማርም የተዘጋጀ ነው። በየቀኑ መልካምንና ክፉን ነገር ሁለቱንም ይማራል። እናንተም በየቀኑ በቃላችሁ፥ በሥራችሁና በምሳሌነታችሁ ታስተምሩታላችሁ።

መጽሐፍ ቅዱስ፡- «ልጅን በሚሄድበት መንገድ ምራው» ይላል፤ ምሳሌ 22፡6። ይህ የእግዚአብሔር ትዕዛዝ ነው። እርሱ ይህን አላፊነት ለወላጆች ሰጥቶአል። በኤፌ. 6፡4 ደግሞ «እናንተም አባቶች ሆይ ልጆቻችሁን በጌታ ምክርና ተግሣጽ አሳድጉአቸው እንጂ አታስቆጡአቸው» ይላል። ቤታችን ልጆችን በሚገባ የምናሳድግበት ቦታ እንዲሆን የሰማዩ አባታችን ዕቅድ ነው።

በቤት ውስጥ ልጆችን የማስተማሩ ሥራ መምራት ያለባቸው አባቶች ናቸው። የሕፃን አእምሮ እንደ አደረጉት የሚሆን ነው። ሸክላ ሠሪው ማሰሮ ለመሥራት ከሚጠቀምበት ጭቃ ጋር ሊወዳደር ይችላል። በሥራና በእቅድ ጭቃው ጠቃሚ የሆነ ዕቃ ተደርጎ ሊሠራ እንደሚችል ወላጆችም ልጆቻቸውን የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ታማኝ ተከታዮች ሆነው እስኪያድጉ ድረስ ሊያሠለጥኑአቸውና ሊያስተምሩዋቸው ይችላሉ።

ወላጆች በእግዚአብሔር ፊት ልጆቻቸውን የማሠልጠን ሥራ ከሕፃንነታቸው እንኳ ቢሆን የመጀመር ኃላፊነት አለባቸው። እግዚአብሔር «ልጅም በሸመገለ ጊዜ ከዚያ ፈቀቅ አይልም» የሚል ቃል ኪዳን ገብቶላቸዋል፤ ምሳሌ 22፡6

**የጢሞቴዎስ ምሳሌነት፡-** በአዲስ ኪዳን ውስጥ ስለ እርሱ ተጽፎ እንደምናገኘው ጢሞቴዎስ ወጣት ሰው ነበር። ደርቤ በምትባል ከተማ ይኖር ነበረ። አንድ ቀን በመንገድ ሲያልፍ አንድ ሰው ሲናገር ለመስማት የተሰበሰቡ ሰዎችን ተመለከተ። በዚያ ቦታ እግዚአብሔር እንደ ፈቃዱ አይሁዳውያንን እንዴት እንደመረጠ እየተናገሩ ጳውሎስና በርናባስ ሕዝቡን በማስተማር ላይ ነበሩ።

ጢሞቴዎስ በጥንቃቄ አደመጠ። እናቱ ኤውንቄና አያቱ ሎይድ ከአይሁድ ታሪክ ውስጥ ጳውሎስና በርናባስ ከሚሰብኩት ጋር ተመሳሳይ የሆኑትን ብዙ ታሪኮች ነግረውታል። የአይሁድ ሕዝብ፣ ሕዝብን ሁሉ የሚያድነው የመሲሑ አያቶች እንዲሆኑ እግዚአብሔር ያቀደ መሆኑን አውቋል።

ጳውሎስ «አዳኙ መሲሕ መጥቶአል፤ ከዳዊት ቤትም ተወልዶአል። ስሙም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው» ሲል ተናገረ። በዚህን ጊዜ ጢሞቴዎስ ጠጋ አለ። ይህ እውነት ሊሆን ይችላል? ለረዥም ጊዜ ቤተ ሰቡ ሲጠብቁት የነበረው መሲሕ ይሄ ነውን? እርሱ በእውነት መጥቶአልን?

ጳውሎስም በመቀጠል «የአይሁድ መሪዎች በኢየሱስ ቀኑበት። ነቢያት የጻፉትና ቅዱሳት መጻሕፍት ምን እንደሚሉ አልገባቸውም ነበር። ኢየሱስን ይዘው ገረፉና በመስቀል ላይ ሰቀሉት» አለ።

ጢሞቴዎስ ይህን ማመን አቃተው። በእርግጥ እግዚአብሔር እርሱ የቀባውን ሊከላከልለት ይችል አልነበረምን? ብሎ ራሱን ጠየቀ።

ጳውሎስ «እግዚአብሔር የሁላችንን ኃጢአት በእርሱ ላይ አኖረ። እርሱም ለእኛ የፋሲካ በግ ሆነ። ለኃጢአታችን መሞት ነበረበት። ከመስቀል ከአወረዱት በኋላ በመቃብር አኖሩት፥ እርሱ ግን መበስበስን አላየም። በሦስተኛውም ቀን እግዚአብሔር በአዲስ ሕይወት ከሞት አስነሳው። አሁን በእርሱ የሚያምኑ ሁሉ የኃጢአት ይቅርታና በክርስቶስ አዲስ ሕይወትን ሊያገኙ ይችላሉ» በማለት ንግግሩን ቀጠለ።

ይህ አዲስ ትምህርት የጢሞቴዎስን ልብ ቀሰቀሰው። እርሱም እራሱ መሲሑን ይጠብቅ ነበረ። አሁን መሲሑ ኢየሱስ ክርስቶስ መጥቶአል። ጢሞቴዎስ ጳውሎስ የተናገረለትን ይቅርታ ማግኘት ፈለገ። ይህን አዲስ ሕይወት ፈለገ። ጢሞቴዎስም በዚያን ቀን ክርስቶስን አመነ። ልቡ በደስታ ተሞላ፤ አዲስ ሕይወትም በውስጡ አገኘ።

ጳውሎስና በርናባስ ለማስተማር ወደ ሌሎች ቦታዎች ሄዱ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ጢሞቴዎስንና በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ያመኑትን ሌሎች ለማበረታታት ተመልሰው መጡ። ጢሞቴዎስ ከእናቱና ከአያቱ ጋር ቅዱሳት መጻሕፍትን ያጠና ነበር። መንፈስ ቅዱስ እየገለጸለት ብዙ ሐቆችን ሊረዳ ቻለ።

ጳውሎስ ጢሞቴዎስን ከእርሱ ጋር ሄዶ ወንጌልን እንዲሰብክ ጠየቀው። በደርቤ የሚገኙት አማኞች ስለ ጢሞቴዎስ መልካምነት ለጳውሎስ ነገሩት። እነርሱም እጃቸውን ጭነውበት ከፍተኛ ጥሪ ላለው አገልግሎት ከጳውሎስ ጋር እንደ ወንጌላዊ እንዲሆን ለዩት። 1ኛ ጢሞ. 4፡14ንና 2ኛ ጢሞ. 4፡5ን አንብቡ። ጢሞቴዎስ ትንሽ ልጅ ከነበረበት ጊዜ ጀምሮ በሚገባ የእግዚአብሔርን ቃል ተምሯል። በመሲሑ በኢየሱስ ክርስቶስም ደግሞ አምኖ አሁን እርሱን ለማገልገል ዝግጁ ሆኖአል።

ለብዙ ዓመታት የጳውሎስ ታማኝ የአገልግሎት ጓደኛው ነበር። ከባድ ኃላፊነቶችን ተቀብሎ በእምነቱ ጸንቶ ቆሞአል። ሌሎች ሲዋዥቁና አንዳንዶችም ወደ ኋላ ሲመለሱ ኢየሱስ ክርስቶስ ላስተማረው የእምነት ትምህርት ጢሞቴዎስ በታማኝነት እንደሚቆም ጳውሎስ ይተማመንበት ነበር።

ጢሞቴዎስ የእናንተ ልጅ ቢሆን ኖሮ ከሐዋርያው ጳውሎስ ጋር እንዲሰብክና እንዲያስተምር ቢጠራ በጣም ደስ እንደሚላችሁ እርግጠኛ ነኝ። በእናንተ በኩል በጥንቃቄ ብታሠለጥኑአቸውና ብትጸልዩላቸው፥ ልጆቻችሁ ደግሞ ጌታን የሚያገለግሉ ሆነው ሊያድጉ ይችላሉ። ልጆቻችሁን ከሕፃንነታቸው ማስተማር ጀምሩ፤ እግዚአብሔርም በልባቸው ውስጥ በቃሉ እንደሚሠራ እመኑት፤ ዕብ. 4፡12።



## ክፍል 1 - ትምህርት 2

## ለልጆቻችሁ ማስተማር ያለባችሁ ነገሮች

የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል:- 2ኛ ጢሞ. 3፡16-17፤ 2ኛ ጴጥ. 1፡21

ዓላማ:- ወላጆች ልጆቻቸውን በሚያስተምሩበት ጊዜ ከእግዚአብሔር ቃል እንዲጠቀሙ ለማነሳሳት።

በቃል የሚጠና ጥቅስ:- «የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል።» 2ኛ ጢሞ. 3፡16።

መግቢያ:- በመዝ. 126/127/፡4 ውስጥ «በኃያል እጅ እንዳሉ ፍላጻች የጎልማስነት ልጆች እንዲሁ ናቸው» የሚለውን ጥቅስ እናነባለን። የቀስቶችና የልጆች መነጻጸር እንግዳ የሆነ ነገር አይደለምን?

ቀስት የአዳኝ መሣሪያ ነው። የቀስቱ እንጨት ቀጥ ያለና ጠንካራ መሆን አለበት። የቀስቱም አናት ከሹሉ ጫፍ ጋር በሚገባ መመጣጠን አለበት። ከዚያ በኋላ አዳኙ ቀስቱን በደጋኑ ላይ አድርጎ በሙሉ ኃይሉ ሊወንጭፈውና በእውነትም ዒላማውን ሊመታ ይችላል።

ቀስቶች የሚሠሩት እንዴት ነው? አዳኙ ቀጥ ያለና ጠንካራ ዘንግ ይፈልጋል። አስተካክሎ ካደረቀው በኋላ ዘይት ይቀባዋል። የቀስቱን አናት በጥንቃቄ ያዘጋጃል። ብረቱ እስኪለሰልስ ድረስ እሳት ውስጥ አስቀምጦት ከአጋለው በኋላ አውጥቶ ትክክለኛ የሆነ ቅርጽ እስኪይዝ ድረስ በመዶሻ ይመታዋል። ከዚያም ጫፉን ይስለዋል። በመጨረሻም አዳኙ የሚኮራበትና የሚመካበት ቀስት ይሆናል።

ልጆችም እንደ ቀስቶቹ ናቸው። ትክክለኛ፥ እውነተኛና ለጌታ ጠቃሚ እንዲሆኑ ከአስፈለገ በብዙ ጥንቃቄ መሠልጠን ያስፈልጋቸዋል። የዚህ ማሰልጠን ዋና ኃላፊነት ያለው በቤተሰቡ አባት ላይ እንደሆነ ተናግረናል፤ ኤፌ. 6፡4። የልጆቹ እናት በዚህ የማሠልጠን ሥራ ውስጥ እርሱን ትረዳዋለች። ነገር ግን ወላጆች ልጆቻቸውን ምን ማስተማር አለባቸው?

የማስተማሪያው መጽሐፍ የእግዚአብሔር ቃል ነው። ልጆችን ለመምሪያ እና ለማሠልጠኛ የእግዚአብሔር ቃል የሆነው መጽሐፍ ቅዱስ እጅግ አስገራሚ የሆነ መሣሪያ ነው። የእግዚአብሔርን ቃል በእምነት ለቤተሰባችን በምናስተምርበት ጊዜ እግዚአብሔር የእነርሱን ሕይወት ለመለወጥ እንደሚጠቀምበት እናውቃለን። ዕብራውያን 4፡12 «የእግዚአብሔር ቃል ሕያው ነውና የሚሠራም ... ነው» ይላል። በሰዎች ልብ ውስጥ ስለሚሠራ ከሌሎች መጻሕፍት የተለየ ሕያው ቃል ነው።

2ኛ ጴጥ. 1፡21 በጥንት ጊዜ ትንቢቶች ወይም ጥንታዊ ጽሑፎች «ከቶ በሰው ፈቃድ» እንደ አልመጡ፥ «ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ተልከው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው» እንደተናገሩአቸው ይገልጻል። ቃሉን እንዲጽፉ እግዚአብሔር ነቢያትን በቅዱስ መንፈሱ ነዳቸው። ዛሬ ለልጆቻችን ማስተማር ያለብን ያንን የእግዚአብሔር ቃል ነው።

2ኛ ጢሞ. 3፡16-17ን አንብቡ። የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፉ ሁሉ ... ይጠቅማል። የእግዚአብሔር መንፈስ በቃሉ ውስጥ ሆኖ ይሠራል። መጽሐፍ ቅዱስ መጀመሪያ

በተጻፈበት ቋንቋ «የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ» የሚለው በዘፍ. 2፡7 ውስጥ ከተጠቀመበት ቃል ጋር ተመሳሳይ ነው። በዚያ ቦታ «እግዚአብሔር አምላክም ሰውን /አዳምን/ . . . በአፍንጫውም የሕይወት እስትንፋስን እፍ አለበት፤ ሰውም ሕያው ነፍስ ያለው ሆነ» ይላል። በተመሳሳይ ሁኔታ እግዚአብሔር መጽሐፍ ቅዱስን እንዲጽፉ በመረጣቸው ሰዎች ውስጥ ቃሉን እፍ አለባቸው።

የእግዚአብሔር ቃል ለአራት ነገሮች ይጠቅማል። በዚህ ላይ እናቁምና እስኪ የዛሬውን በቃል የሚጠናውን ጥቅስ እንድገመው። የእግዚአብሔር ቃል ጠቃሚ የሆነው ለምን ዓይነት አራት ነገሮች ነው?

ለትምህርት ይጠቅማል። ለልጆቻችንና በቤታችን ላሉት ሁሉ ልናስተምረው ይገባናል። በምናስተምርበት ጊዜ ቃሉ እራሱ የሚሰሙትን ይገስጻል፥ ይወቅሳል። በሕይወታችን ውስጥ ያለውን ጉድለትና ድካም ያሳየናል። ክርስቶስም ስለ ኃጢአታችን እንድንናዘዝና ይቅርታም እንድንቀበል ብርታትን ይሰጠናል፤ 1ኛ ዮሐ. 1፡9።

እንደገና ደግሞ የእግዚአብሔር ቃል ያስተካክለናል። ማስተካከል ማለት ወደ ትክክለኛው መንገድ መመለስ ማለት ነው። በጫካ ውስጥ በተሳሳተ መንገድ ብትሄዱ ትጠፋላችሁ ወይም የማታውቁት ሥፍራ ትደርሱ ይሆናል። ሆኖም መንገዱን የሚያውቅ ጓደኛ ካላችሁ ወደ ትክክለኛው መንገድ ይመራችኋል። የእግዚአብሔርን ቃል ስናነብና ስንታዘዝ እርሱም ለእኛ እንደዚሁ ያደርግልናል።

ምክር ሲያስፈልጋችሁ ወደ ማን ነው የምትሄዱት? አብዛኛውን ጊዜ በዕድሜ ከእናንተ ከፍ ያሉ ጓደኞቻችሁ ጥሩ ምክር ሊሰጧችሁና ችግሮች በሚያጋጥሙአችሁ ጊዜያት ሊረዱዋችሁ ይችላሉ። ይሁን እንጂ ምክር ለማግኘት የሚኬድበት ከሁሉ የበለጠው ቦታ የእግዚአብሔር ቃል ነው። የእግዚአብሔር ቃል በጽድቅ ላለው ምክር ይጠቅማል።

ሙሴ በምድረ በዳ ይኖሩ የነበሩትን የእሥራኤል ትውልድ ይህንን የእግዚአብሔርን ቃል በጥንቃቄ አስተምሯቸዋል። እግዚአብሔር ለእሥራኤል ልጆች እንዲከተሏቸው አሥርቱን ትእዛዛትና ሌሎችን ብዙ መመሪያዎች በሰጠበት ጊዜ እነርሱም ከሙሴ ጋር ነበሩ። ያም ሆኖ የእነርሱ ልጆች ደግሞ እንዲማሩ አስፈለገ። እግዚአብሔር ሙሴን ምን ማድረግ እንዳለበት በትክክል ነገረው። መጽሐፍ ቅዱሳችሁን ግለጡና ዘዳግም 31፡11-13ን አውጡ። «እሥራኤል ሁሉ በአምላክ በእግዚአብሔር ፊት ይታይ ዘንድ እርሱ በመረጠው ሥፍራ ሲከማች፥ ይህን ሕግ በእሥራኤል ሁሉ ፊት በጆሮው አንብበው። ይሰሙና ይማሩ ዘንድ፥ አምላካችሁንም እግዚአብሔር ይፈሩ ዘንድ፥ የዚህንም ሕግ ቃሎች ሁሉ ጠብቀው ያደርጉ ዘንድ ሕዝቡን ወንዶችንና ሴቶችን ሕፃናትንም በአገራችሁ ደጅ ያለውንም መጻተኛ ሰብስብ። የሕግን ቃላት የማያውቁ ልጆቻቸውም ዮርዳኖስን ተሻግራችሁ ልትወርሱአት በምትሄዱበት ምድር በምትኖሩበት ዘመን ሁሉ ይስሙ፥ አምላካችሁን እግዚአብሔርንም መፍራት ይማሩ።»


ሙሴ ለሕዝቡ መሪዎች የእግዚአብሔር የሕጉ ቃል ሕዝቡ ሁሉ እንዲሰሙት በእሥራኤል ሁሉ ፊት እንዲያነቡት ነገራቸው። እንዲሰሙ የተመረጡት እነማን ነበሩ? /ወንዶች፥ ሴቶች፥ ሕፃናትና በሰፈሩ ውስጥ ያሉ እንግዶች በሙሉ።/

የሕጉ መነበብ ዋናው ዓላማ ሕዝቡ በሙሉ እንዲሰሙትና እግዚአብሔርን መፍራት እንዲማሩ ነው። ይህም የተቀደሰ ፍርሐት ነው ምክንያቱም ሰሚውን እግዚአብሔርን የማስደሰት

ፍላጎት እንዲኖረውና እርሱን እንዳያሳዝን እንዲፈራ ያደርገዋል። ልጆቻችሁን የእግዚአብሔርን ቃል በጥንቃቄ በማስተማር፥ በልባቸው ውስጥ ይህን ቅዱስ የሆነ ፈሪሃ እግዚአብሔር ታሳድራላችሁ። ከዚያ በኋላ ክፉ ነገር እንዲያደርጉ በሚፈተኑበት ጊዜ እግዚአብሔርን ለማሳዘን ስለማይፈልጉ ትክክለኛውን መንገድ ይመርጣሉ። ዮሴፍ ጽኑ ፈተና በገጠመው ጊዜ ኃጢአትን ከማድረግ የጠበቀው ይህ ዓይነቱ ፍርሃት ነበረ። ስለ ዮሴፍ በኦሪት ዘፍጥረት 39፡8-10 ውስጥ የተጻፈውን አንብቡ።

«ሁሉንም ነገር በአንድ ቀን ልናስተምራቸው አንችልም፤ እንዴት አድርገን መጀመር እንችላለን?» ትሉ ይሆናል። ይህ ጥሩ ጥያቄ ነው። በሚቀጥለው ትምህርት ውስጥ እንዴት አድርጋችሁ ማስተማር እንደምትችሉ ጥቂት አሳቦችን ልንሰጣችሁ እንሞክራለን።

መጽሐፍ ቅዱስ ሕያው የሆነ የእግዚአብሔር ቃል ስለሆነ አንብቡትና ለልጆቻችሁ አብራሩላቸው። እግዚአብሔር በቃሉ በኩል ልጆቻችሁ ትክክለኛ፥ እውነተኛና ለአዳኙ ቀስቱ ጠቃሚ መሣሪያ እንደ ነበረ እንዲሁም ለጌታ የሚጠቅሙ እንዲሆኑ በሕይወታቸው ውስጥ በቃሉ በኩል ይሠራል። ልጆቻችሁን በጥንቃቄ ከማስተማርና ለእግዚአብሔር የሚያስደስቱ ሆነው እንዲያድጉ ከማድረግ የበለጠ ምን ዓይነት ታላቅ ደስታ ይኖራችኋል!



# ክፍል 1 - ትምህርት 3

## ልጆቻችሁን እንዴት እንደምታስተምሩ

ዓላማ፡- ወላጆች የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርታቸውን ለልጆቻቸው አስደሳችና ከፍላጎታቸው ጋር የሚስማማ አድርገው እንዲያቀርቡት ለማበረታታት።

በቃል የሚጠና ጥቅስ፡- «እኔም ዛሬ አንተን የማዝዘውን ይህን ቃል በልብህ ያዝ ለልጆችህም አስተምረው» ዘዳግም 6፡6-7

መግቢያ፤ ሙሉነሽ ከቤትዋ በስተጀርባ አንድ ሥራ ትሠራ ነበር። እርሷም ከወዲያ ወዲህ እየተመላለሰች መዝሙር ስትዘምር እናቷ ይሰሙዋት ነበር። «ምን እያደረገች ነው?» ብለው በመገረም የምታደርገውን ለመመልከት ቀስ ብለው ወደ በሩ ሄዱ። የሦስት ዓመቷ ሕፃን ሙሉነሽ እራሷ ከእርጊ ብጣሽ ጨርቅ አሻንጉሊት ሠርታ በጀርባዋ አዝላ እናትዋ ልጅ ሲያለቅስባቸው እንደሚያደርጉት እርሷም ልጅዋን ለማስተኛት ወዲያ ወዲህ እያለች መዝሙር ትዘምርላት ነበር። የሙሉነሽ እናት ሳቅ አሉና «እኔም እኮ እሷን የማክል ልጅ በነበርኩበት ጊዜ እንዲህ አድርጌያለሁ» ብለው አሰቡ።

ልጆች ትልልቅ ሰዎች የሚሠሩትን መሥራት ደስ ይላቸዋል። ካዩና ከሰሙ በኋላ ያንኑ ለማድረግ ይሞክራሉ።

## ልጆች የሚማሩት እንዴት ነው?

<u>በመስማት ይማራሉ።</u>

ልጆች ከሚሰሙት ነገር ይማራሉ። ታሪኮችን መስማት ይወዳሉ። ስለዚህ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉትን አስገራሚ የሆኑትን የወንዶችንና የሴቶችን፥ የወንዶችና የሴቶች ልጆችን ታሪኮች ተርኩላቸው። አንዳንዶቹ ትክክለኛ የሆኑትን ነገሮች እንዴት እንዳደረጉና ጌታን እንዳስደሰቱት አሳዩአቸው። አንዳንዶቹ ደግሞ የተሳሳቱ ነገሮችን እንዳደረጉና ውጤታቸውም ምን እንደነበረ ንገሩዋቸው። ለልጆቻችሁ የምትነግሯቸውን ታሪኮች በዝርዝር እስከታውቋቸው ድረስ ከመጽሐፍ ቅዱሳችሁ ውስጥ ደጋግማችሁ በማንበብ አዘጋጁ ለእናንተ አባቶቻችሁ እንደነገሯችሁ ታሪክ አድርጋችሁ እናንተም በእውነተኛ ኢትዮጵያዊ አቀራረብ አዘጋጅታችሁ ንገሩአቸው። ታሪኩን በታሪኩ ውስጥ እንዳሉት የተለያዩ ሰዎች አድርጋችሁ እናንተም ድምፃችሁን እየለዋወጣችሁ አቅርቡ። ለልጆቻችሁ ሊገባቸው በሚችሉ ቃላት ተጠቀሙ። እነርሱም ይወዱታል።

<u>በማየት ይማራሉ።</u>

ልጆች አንድን ነገር በሚሰሙበት ጊዜ ቢመለከቱት የበለጠ ሊማሩትና ሊያስታውሱት ይችላሉ። ታሪኩን በምትናገሩበት ጊዜ በታሪኩ ውስጥ ያሉትን ነገሮች በተግባር ልታሳዩ ትችላላችሁ። ከታሪኩ ጋር የሚሄድ ሥዕል ካላችሁ ለልጆቻችሁ አሳዩዋቸውና በሥዕሉ ውስጥ የሚገኙትን ነገሮች አብራሩላቸው። ወይም ለማስተማሪያችሁ አንድ ነገር እንደ ምሳሌ አድርጋችሁ ማቅረብ ትችላላችሁ። ኢየሱስ የሰናፍጭን ፍሬ ከእምነት ጋር እንዴት እንዳነጻጸረው በምታስተምሩበት ጊዜ የሰናፍጭን ፍሬ አሳዩአቸው። ስለ ዘሪውና ዘሮቹ ስለወደቁባቸው የመሬት ዓይነቶች በምታስተምሩዋቸው ጊዜ ወደ ውጪ አውጥታችሁ የተለያዩትን የመሬት ዓይነቶች አሳዩዋቸው።

## በጥያቄና በመልስ ይማራሉ።

ልጆቹ በንግግርም ደግሞ ይማራሉ። እንደዚያም ሲሆን ለጥያቄዎች መልስ በመስጠት ብዙ ይማራሉ ማለት ነው። በአሳባቸው ውስጥ ያለውን በቃላት እንዲገልጹት ያደርጋቸዋል። አንድ ታሪክ ከነገራችኋቸው በኋላ ታሪኩን የሚመለከቱ ጥያቄዎችን ጠይቁዋቸው። የሰሙትን እንዲያስታውሱ ይረዳቸዋል። እናንተም ምን ያህል እንደሰሙአችሁ እንድታውቁ ይረዳችኋል። ጥያቄ ይኖራቸው ይሆናል። ይጠይቁና እናንተም መልስ ስጡአቸው።

## ነገሮችን በማድረግ ይማራሉ።

ልጆች አንድ ቦታ ከመቀመጥ አንድ አንድ ነገር መሥራት ይወዳሉ። በታሪኩ ውስጥ ያሉትን ነገሮች በቲያትር መልክ እንዲያሳዩ አድርጓቸው። ምናልባት መናገር ያለባቸውን እንዲናገሩ መምራት ወይም መገፋፋት ይኖርባችኋል። ለምሳሌ የታመመውን ጓደኛቸውን ወደ ኢየሱስ ስላመጡት አራት ሰዎች ለድራማ ስታስለጥኑአቸው ከወንድሞቻቸው አንዱን እንዲሸከሙት አድርጉ። ኢየሱስ የተናገራቸውን ቃላት ይናገሩ፥ ከዚያም በመጨረሻ ላይ ሁሉም ሰው «እንዲህ ያለ ነገር ከቶ አይተን አናውቅም» እንዲሉ አድርጉ። ይህ ታሪክ በማርቆስ 2፡1-12 ውስጥ ይገኛል።

በሌላ ጊዜ ደግሞ በታሪኩ ውስጥ የተደረገውን ነገር በሥዕል እንዲገልጹ ልታደርጓቸው ትችላላችሁ። ማታ ከሥራ ወደ ቤት ስትመለሱ እንዲያሳዩአችሁ ንገሩአቸው። ከሥራ ስትመለሱ እንዲያሳዩአችሁ መጠየቅን አትርሱ። ምናልባት በግድግዳ ላይ ለመስቀል በንጹሕ ወረቀት ላይ ጥቅስ በግሉህ ፊደላት መጻፍ ይወዱ ይሆናል። የእግዚአብሔር ቃል የሚነግረን እንዲህ እንድናደርግ ነው። ዘዳግም 6፡4-9ን አንብብ።

ልጆች፡-

በመስማት ብቻ ከትምህርቱ ከመቶ አሥሩን እጅ

በመስማትና በማየት ከትምህርቱ ከመቶ ስድሳውን እጅ

በመስማት፥ በማየትና በመናገር ከመቶ ሰባውን እጅ

በመስማት፥ በማየት፥ በመናገርና በማድረግ ከመቶ ዘጠናውን እጅ

ሊማሩ እንደሚችሉ ሊቃውንት ይናገራሉ።

## የተለያዩ ዕድሜያት ያላቸው ልጆች ጸባያት

1. አምስትና ስድስት ዓመት ዕድሜ ያላቸው ልጆች መዘመር ይወዳሉ። መዝሙሮችን በድርጊት በማሳየት ወይም እጆቻቸውን በማጨብጨብ ቶሎ መማር ይችላሉ። በቡድኑ ውስጥ አንድ ዓይነት ድርሻ እንዲኖራቸው ቢደረግ የቡድኑ አካል እንደሆኑ ሊሰማቸው ይችላሉ። በማስታወስ በኩል ደግሞ አጫጭር ጥቅሶችን በቃላቸው ማጥናት ይችላሉ። እንደዚህ ያሉ አንዳንድ ነገሮችን እንዲያደርጉ ዕድል ስጧቸው።

2. ወደ ትምህርት ቤት መሄድ የጀመረው ወይም የጀመረችው ወንዱ ወይም ሴቷ ልጃችሁ ማንበብ ለመማር ጀምሯል ወይም ጀምራለች ማለት ነው። አንድ ወይም ሁለት ጥቅሶች እንዲያነብ ብትጠይቁት ወይም ብትጠይቋት በእናንተ መሃከል ጠቃሚ የሆነ ቦታ እንደ

ሰጣችሁት ወይም እንደሰጣችኋት ይሰማዋል ወይም ይሰማታል። ረዥም የሆኑት ቃላት አልነበብ ብለው ቢያስቸግሩ እንዲያነብ ወይም እንድታነብ ሊታደፋፍሩ ትችላላችሁ።

3. ዕድሜያቸው ከ9-12 የሆኑ ልጆች ጥሩ የማስታወስ ችሎታ አላቸው። ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ረዥም የሆኑትን ምንባቦች በቃላቸው ማስታወስ ይችላሉ። ከመዝሙረ ዳዊት ውስጥ በቃላቸው እንዲያጠኑ አንድ መዝሙር ስጧቸው። አጥንተው ከጨረሱት በኋላ በእነርሱ የተደነቃችሁ መሆኑን ግለጹላቸው። የጀግኖችን ታሪክ መስማት ስለሚወዱ የዳዊትን፥ የዳንኤልን፥ የጳውሎስንና የሌሎችንም ታሪኮች ንገሩአቸው።

4. በቤተሰባችሁ ውስጥ ያሉት ወጣቶች ለራሳቸው ማሰብ በመጀመር ላይ ናቸው። በአንዳንድ ነገሮች ላይ እንድትወያዩ አደፋፍሩአቸው። ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለሚያነቧቸው አንዳንድ ነገሮች ያላቸውን አሳብ እንዲገልጹ አድርጓቸው። ለጥያቄዎቻቸው አብራችሁ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ መልሶችን ለማግኘት ሞክሩ።

በየቀኑ ሰዓት ወስኑ።

«እኔ ይህን ሁሉ ለማድረግ ጊዜ የት አለኝ? እኔ ሥራ የሚበዛብኝ ሰው ነኝ። ባለቤቴ ከልጆች ጋር ስለምትውል እርሷ ትሥራው» ትሉ ይሆናል።

በእርግጥ ሚስቶቻችሁ ከእናንተ ይበልጥ ብዙ ጊዜ ከልጆች ጋር ያጠፉ ይሆናል። እናቶች ልጆቻችሁ ከእናንተ የተማሩትን ትምህርቶች ያስታውሷቸዋል። ከመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮች ውስጥ ያገኟቸውን ትምህርቶች በዕለታዊ ሕይወታቸው በተግባር እንዲገልጹት ሊመሩዋቸውና ሊረዱዋቸው ይችላሉ። ዘዳግም 6:7 «በቤትህም ስትቀመጥ፥ በመንገድም ስትሄድ፥ ስትተኛም፥ ስትነሣም ተጫወተው» እንደሚለው ለማድረግ ይችላሉ። ቢሆንም የመምራቱን ሥራ መሥራት ያለባችሁ አባቶች ናችሁ። ልጆቻችሁ እግዚአብሔርን የሚወዱና የሚፈሩ ሆነው እንዲያድጉ ቅን ፍላጎት እንዳላችሁ ሁሉ ጠቢብ በመሆን በየቀኑ የእግዚአብሔርን ቃል አብራችሁ የምታነቡበትን ጊዜ ወስኑ። ምናልባት ከቁርስ በኋላ ጥሩ ጊዜ ሊሆን ይችላል። ወይም ማታ የእራት ሰዓት እስኪደርስ ባለው ጊዜስ ቢሆን? ምናልባት ለቤተሰባችሁ ከእራት በኋላ ያለው ጊዜ የተሻለ ሊሆን ይችላል። ልጆቻችሁን በዙሪያችሁ ሰብስባችሁ ይህችን ጊዜ ቤተሰብ በሙሉ ከጌታ ጋር የምትሆኑባት ጊዜ አድርጓት። ይህች በየዕለቱ የምታደርጓት የፀሎና ጊዜ እጅግ በጣም የምትደሰቱባት እና የተለየች ሰዓት ሆና ታገኟታአላችሁ። ከዚያ በኋላ አብራችሁ ጸልዩ ያን ጊዜ እግዚአብሔር እናንተን፥ ቤታችሁንና ቤተ ሰባችሁን ይባርካል።

# ክፍል 2

# ትምህርት 4-6

## ልጆችን የዘወትር ልማድ እንዲኖራቸው ማሠልጠን

የክፍሉ ዓላማ፡- የማሠልጠኑን ሥራ መደበኛ ልማድ አድርጎ የማሰልጠኑን ጥቅምና ከእነዚህም ልማዶች አንዳንዶቹ ምን መሆን እንዳለባቸው ለማሳየት።

የክፍሉ ጥቅስ፡- «ለእነርሱ ለዘለዓለም ለልጆቻቸው መልካም ይሆንላቸው ዘንድ እንዲፈሩኝ ሁል ጊዜም ትዕዛዜን ሁሉ እንዲጠብቁ እንዲህ ያለ ልብ ምነው በሆነላቸው?» ዘዳግም 5፡29።

## ክፍል 2 - ትምህርት 4

### ጸሎት

ዓላማ፡- የጸሎትን መሠረታዊ መመሪያዎች ለማስተማርና ወላጆች ልጆቻቸው መጸለይን እንዲያስተምሩ ለማበረታታት።

በቃል የሚጠና ጥቅስ፡- «ወደ እኔ ጩኽ እኔም እመልስልሃለሁ፤ አንተም የማታውቀውን ታላቅና ኃይለኛ ነገርን አሳይሃለሁ?? ኤርምያስ 33፡3።

መግቢያ፡- «ልጆቻችሁ ስንት ዓመት ሆኖአቸዋል?» ልጆቻችን ገና ትንንሽ ናቸው ትሉ ይሆናል። ነገር ግን ይህ ዕድሜ ልጆችን እንዲጸልዩ ማስተማርን ለመጀመር ጥሩ ጊዜ ስለሆነ መልካም ነው።

«የልጆቼ ዕድሜ የተለያየ ነው፥ አንዳንዶቹ ትንንሾች ናቸው፤ አንዳንዶቹ ደግሞ ትልልቆች ናቸው» ትሉ ይሆናል። ያም ደግሞ መልካም ነው። ለመጀመር ዘግይታችኋል ማለት አይደለም። ከልጆቻችሁ ጋር ጸልዩ፥ እነርሱም እንዲጸልዩ አበረታቱዋቸው።

በማንኪያ የተፈጨ ምግብ ለሚመገበው ሕፃን ልጅ እንኳ መብላት ከመጀመሩ በፊት ጸሎት ማድረግ እንዳለበት ማስተማር ለመጀመር ጊዜው ገና ነው ማለት የለባችሁም። ሁለቱንም ትንንሽ እጆቹን በእጃችሁ ውስጥ ይዛችሁ ዓይናችሁን ጨፍናችሁ «ጌታ ሆይ፥ ስለ ልጄ ምግብ አመሰግንሃለሁ። አሜን» ብላችሁ ጸልዩ። የምትጸልዩባቸውን ቃላት በየጊዜው መለወጥ ትችላላችሁ፤ ነገር ግን ስትጸልዩ በጣም ቀስ ብላችሁ፥ በጣም ቀላልና ግልጽ አድርጋችሁ መናገር አለባችሁ። ከጥቂት ቀናት በኋላ ምግብ መመገብ ከመጀመሩ በፊት እራሱ ዐውቆ አንገቱን ማቀርቀርና እጆቹን ማጠፍ ይጀምራል። መናገር በሚጀምርበት ጊዜ እናንተን በመከተል መጸለይ ይችላል። በዚህ መንገድ ልጃችሁን እስከ ሕይወቱ መጨረሻ የሚቆይ ልማድ አስተምራችሁታል፥ ገና ከልጅነቱም እግዚአብሔር በሰማይ ሆኖ ጸሎትን እንደሚሰማና እንደሚመልስ አሳውቃችሁታል ማለት ነው።

## ጸሎት ምንድነው?

ቱቱ አዲስ ቀሚስ ማግኘት በጣም ፈለገች። የነበራት ቀሚስ በጣም ተቀዳዷል። አባቷ ጎበዝ ሠራተኛ እንደሆነና ለቤተሰቡ የሚያስፈልገውንም ለማግኘት እንደሚጣጣር ታውቃለች። ስለዚህ አባቷን ላለመጠየቅ፥ በመጠየቅ ፋንታ ግን ለመጸለይ ወሰነች። ሁልጊዜ ማታ ማታ አልጋዋ ውስጥ ከመግባትዋ በፊት ትንበረከክና አዲስ ቀሚስ የሚያስፈልጋት መሆኑን ለእግዚአብሔር ታስታውስ ነበረ።

የዘመን መለወጫ ዕለት እርሷን ደስ እንዲላት አባቷ አንድ የተጠቀለለ ነገር ይዞላት መጣ። የተጠቀለለውን ከፈተና የገዛላትን ቆንጆ ቀሚስ አሳያት። ቀሚሱ ልክ እንደ እናቷ ቀሚስ ነጭና ዙሪያውም በቀለማት የተዋበ ጥለት ያለበት በልከዋ የተሰፋ ነበረ። በጣም ተደሰተች። በቤቱ ዙሪያ እየዘለለች ቀሚስዋን ለሰው ሁሉ ማሳየት ጀመረች።

የዚያን ዕለት ማታ እናትዋ ቱቱ ሳትጸልዩ እንደተኛች ተመለከተችና «ቱቱ የተኛሽው እኮ ሳትጸልዩ ነው!» ብላ አስታወሰቻት።

ቱቱም «አይ አልረሳሁትም፥ ቀሚስ ስለተገዛልኝ በጣም ደስ ብሎኛል። ሌላ ምንም ነገር አልፈልግም» ብላ መለሰች። ተመልከቱ፥ ቱቱ ያሰበችው ጸሎት እግዚአብሔርን አንዳንድ ነገሮች እንዲሰጣት ብቻ መለመኛ አድርጋ ነው። ነገር ግን እውነተኛው ጸሎት ከዚህም በላይ ነው።

## ጸሎት አምልኮትና ማመስገኛ ነው።

ጸሎት እግዚአብሔርን በኢየሱስ ስም ለማምለክና ለማመስገን ወደ እርሱ ዘንድ መቅረብ ነው። እናንተም ኢየሱስ ክርስቶስን በእውነት እንደ አዳኛችሁ አድርጋችሁ የተቀበላችሁት ከሆነ እግዚአብሔር አባታችሁ ነው! ዮሐ. 1፡12። ቅዱሱ፥ ከሁሉ ይልቅ ኃይልን የተሞላው፥ ጠቢቡና የዓለም ሁሉ ፈጣሪ የሆነው የእናንተ አባት ነው።

በጸሎት በማናቸውም ጊዜ ወደ እርሱ ልትመጡ ትችላላችሁ። መዝሙር 94/95/፡ 1-7 አንብቡ። በእነዚህ ጥቅሶች ውስጥ ዳዊት በምን ዓይነት ሁኔታ እግዚአብሔርን ማመስገን እንዳለብንና ስለ ምን ልናመሰግነው እንደሚገባ አንዳንድ አሳቦችን ይሰጠናል። ልናመልከው የሚገባን እርሱን ብቻ መሆን አለበት። ማቴ. 4፡ 10ን አንብቡ። በዙሪያችን የእርሱን ታላቅነትና ፍቅሩን የሚያረጋግጡ ብዙ ማስረጃዎችን እያየን ሳናቋርጥ እናመስግነው። መዝ. 33/34/፡ 1፥ 1ኛ ተሰ. 5፡ 18

## ጸሎት ኑዛዜ ነው።

አባታችን እግዚአብሔርን በጸሎት ስንቀርበው ስለ ታላቅነቱ፥ እንደዚሁም ስለ ቅድስናውና ስለ ኃይሉ በአንዳንድ ነገሮች በተረዳን ቁጥር እኛ ምን ያህል ኃጢአተኞች መሆናችንን እንገነዘባለን። በሕይወታችን ውስጥ የእርሱን የማይመስሉ ብዙ ነገሮችን እናያለን። ምንም እንኳ በክርስቶስ አምነን የኃጢአት ይቅርታ በማግኘት ልጆቹ ብንሆንም በየቀኑ ከኃጢአታችን መንጻት ይኖርብናል። 1ኛ ዮሐ. 1፡6-10ን አንብቡ። ትክክል እንዳልሆንና እርሱንም እንደማያስደስት ስንረዳ ማናቸውንም ኃጢአት እንናዘዛለን። በተጨማሪም መዝ. 65/66/፡ 18ን አንብቡ።

ጸሎት ልመና ነው።

ቶቶ የሚያስፈልጋትን ነገር ከእግዚአብሔር መጠየቋ ትክክለኛ ነበረች። እግዚአብሔር እናንተን «ለምኑ ይሰጣችሁማል፥ ፈልጉ ታገኙማላችሁ፥ መዝጊያን አንኳኩ ይከፈትላችሁማል» ማቴ. 7፡7 በማለት ወደ ጸሎት ጋብዞአችኋል። አሁን ማቴ. 7፡9-11ን አንብቡ። በሰማያት ያለው አባታችን ለሚለምኑት መልካም ነገርን መስጠት ደስ እንደሚለው ትመለከታላችሁ።

በማቴዎስ ስድስት ውስጥ ምን እንበላለን ወይም ምን እንጠጣለን ወይም ምን እንለብሳለን ብለን መጨነቅ እንደሌለብን ተነግሯል። ማቴ. 6፡25-32ን አንብቡ። እርሱ የሚያስፈልገንን ሁሉ ያውቃል! የሚያስፈልገንንም ሊሰጠን ቃል ገብቶልናል። እርሱ በእውነት ከእኛ የሚፈልገው በመጀመሪያ መንግሥቱንና ጽድቁን እንድንፈልግ ነው! ከዚያ በኋላ የሚያስፈልገንን ሁሉ እንደሚሰጠን ተናግሯል። ፊልጵስዩስ 4፡19 «አምላኬም እንደ ባለጠግነቱ መጠን በክብር በክርስቶስ ኢየሱስ የሚያስፈልጋችሁን ሁሉ ይሞላባችኋል» ይላል።

ስለዚህ የሚያስፈልጉንን ነገሮች ልንጸልይና ልንጠይቅ እንችላለን። ስለ እነርሱም መጨነቅና መጠበብ የለብንም ማለት ነው። አምላካችን የሚያስፈልገንን ሁሉ በሰፊው ሊሰጠን ይችላል። መዝ. 49/50/፡10-12ን አንብቡ።

## እንዴት መለመን እንዳለብን

### እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ

1ኛ ዮሐ. 5፡14 «እንደ ፈቃዱ አንዳች ነገር ብንለምን ይሰማናል» በማለት ያስታውሰናል። ይህም እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ብንጸልይ ጸሎታችንን ሰምቶ ይመልስልናል ማለት ነው። እንዴት አድርገን ፈቃዱን ማወቅ እንችላለን? እርሱ ፈቃዱን በቃሉ በኩል ይገልጽልናል። ለምሳሌ በማርቆስ 16፡15 ውስጥ ወደ ዓለም ሁሉ እንድንሄድና ለፍጥረት ሁሉ እንድንመሰክር ነግሮናል። ስለዚህ ይህንን በምናደርግበት ጊዜ እንዲረዳንና ስለምንመሰክርላቸው ሰዎች ስንጸልይ በፈቃዱ ውስጥ ሆነን እንደምንጸልይ እናውቃለን። እንዲሁም በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ አንድ ወንድ ወይም ሴት ልጅ እንዲጠፋ ወይም እንድትጠፋ እግዚአብሔር ፈቃዱ አለመሆኑን ደግሞ እናነባለን! ማቴ. 18፡14። ስለ ወንዶች ልጆችና ስለ ሴቶች ልጆች ስለ ትልልቆችም ደግሞ እንዲድኑ በምንጸልይበት ጊዜ እንደ ፈቃዱ የምንጸልይ መሆናችንን እናውቃለን። ስለዚህ እንደ ፈቃዱ መጸለይ እንድንችል የእግዚአብሔርን ቃል ማጥናት ያስፈልገናል።

በሁለተኛ ደረጃም እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ለመጸለይ እንዲረዳን በመንፈስ ቅዱስ መታመን ይኖርብናል። እርሱ እግዚአብሔር ነው። በእግዚአብሔር ፈቃድ ውስጥ እንዴት መፀለይ እንደምንችል፥ መንፈስ ቅዱስ ሊመራንና ሊረዳን ይፈልጋል። (ሮሜ 8፡26ና 2ኛ ጴጥ. 1፡21ን አንብቡ።

### በኢየሱስ ስም

ኢየሱስ እራሱ «አብ በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ ይሰጣችኋል! ... ደስታችሁ ፍጹም እንዲሆን ለምኑ ትቀበሉማላችሁ» ብሏል፥ ዮሐንስ 16፡23-24። ኢየሱስ ልባችን በእርሱ ደስታ እንዲሞላ ይፈልጋል። እግዚአብሔር አብ የምንፈልገውን ነገር እንዲሰጠን በኢየሱስ ስም ልንለምነው እንችላለን! ያን የፈለግነውንም ነገር እንቀበላለን።

### በእምነት

መጽሐፍ ቅዱስ «ያለ እምነት እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት አይቻልም፤ ወደ እግዚአብሔር የሚደርስ እግዚአብሔር እንዳለ ለሚፈልጉትም ዋጋ እንዲሰጥ ያምን ዘንድ ያስፈልገዋል ይላል፤ ዕብ. 11፡6። በጸሎት ወደ እግዚአብሔር በምንቀርብበት ጊዜ እርሱን የምንጠይቀውን ነገር ሊያደርግልን የሚችል መሆኑን ማመን አለብን። ያዕ. 1፡6-7ን አንብቡ። ለጸሎቶቻችንም መልስ አድርጎ ለእምነታችን ዋጋ ይሰጣል። እምነት ምንድነው? እግዚአብሔርን ማመን ነው። እግዚአብሔርን ቃሉ እንደሚናገረው አድርጎ መቀበል ነው። የተናገረውን እንደሚፈጽም ማወቅና ማመን ነው። እምነት ከስሜታችን ጋር ምንም ግንኙነት የለውም፤ ግንኙነት ያለው እግዚአብሔር በቃሉ ውስጥ ከተናገረው ጋር ብቻ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ በእምነት መኖርና ማደግ እንዳለብን ይነግረናል።

### ጸሎት ምልጃ ነው።

ክርስቲያን እንደመሆናችን መጠን አንዳችን ለአንዳችን የመጸለይ መብት አለን። ኤፌ. 6፡18-19ን አንብቡ። ጳውሎስ በኤፌሶን ያሉትን ክርስቲያኖች ለቅዱሳን ሁሉና ለእርሱም ጭምር እንዲጸልዩ ይጠይቃቸዋል። እንዲሁም ስለምን መጸለይ እንዳለባቸው ይነግራቸዋል። ወንጌልን በሚያስተምርበት ጊዜ ድፍረት እንዲኖረው እንዲጸልዩለት ይፈልጋል።

በየቀኑ ከልጆቻችሁ ጋር ጸልዩ። በኅብረት ለምትጸልዩት ጸሎት መልስ ስለሚሰጣችሁ አመስግኑት። በልጆቻችሁ ፊት ኃጢአታችሁን ለእግዚአብሔር በግልጽ ለመናዘዝ አትፍሩ። በንጽሕና ለመኖር ያላችሁን ፍላጎት ያከብሩታል፤ ይከተሉአችሁማል። በኅብረት የሚጸልይ ቤተሰብ ደስተኛ ነው።



## ክፍል 2 - ትምህርት 5

## በግል ከእግዚአብሔር ጋር የመሆኛ ጊዜ

*ዓላማ:- ወላጆች ልጆቻቸው በየቀኑ የእግዚአብሔርን ቃል በሚያነቡበት ጊዜ እንዴት አድርገው እንደሚመሯቸው ለማሳየት።*

በቃል የሚጠና ጥቅስ:- «ቃልህ ተገኝቶአል እኔም በልቼዋለሁ ... **ቃልህ ሐሤትና የልብ** ደስታ ሆነኝ።» ኤርሚያስ 15:16

*መግቢያ:- አቶ ሰሎሞንና ቤተሰቡ በየቀኑ ማታ ማታ ተሰብስበው የእግዚአብሔርን ቃል የሚያነቡበትና የሚጸልዩበት የጥሞና ጊዜ አላቸው።*

አቶ ሰለሞን ቤተሰቡን በዙሪያው ከሰበሰባቸው በኋላ የጠፋውን ልጅ ታሪክ ተረከላቸው። ከዚያም «አባትየው ስንት ልጆች ነበሩት?» ብሎ ጠየቀ።

ወዲያው ዕድሜው 12 ዓመት የሆነው የአቶ ሰሎሞን ልጅ አበራ ለመመለስ ተጣድፎ «እኔ! ልመልስ! እኔ! እኔ ልመልስ!» እያለ እጁን አወጣ። አቶ ሰለሞንም ከራሱ ቀና በማለት የመፍቀድ ምልክት አሳየው። እርሱም «ሁለት ልጆች ነበሩት» ሲል መለሰ።

«መልሱን በየትኛው ጥቅስ ነው ያገኘኸው?» ሲል ጠየቀው።

አበራም:- ከሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 15 ቁጥር 11 ነው «አንድ ሰው ሁለት ልጆች ነበሩት» ይላል ሲል መለሰ።

አባትዮውም ልጁ ችሎታ ያለው መሆኑን የሚያረጋግጥለት ማስረጃ ስላገኘ ኩራት እየተሰማው: «ልክ ነህ፤ እስኪ ቁጥር 12ንና 13ን ደግሞ ለእኛ አንብብልን» አለው። አበራ የሚያነበውን በሚገባ እየተረዳው ለሌሎችም ግልጽ እንዲሆን ደኅና አድርጎ አነበበው።

በዚያ ምሽት ከጥሞና ጊዜያቸው በኋላ ትናንሾቹ ልጆች ወደ መኝታቸው እንደሄዱ አቶ ሰለሞን ቁጭ ብሎ ያስብ ነበር። አበራ እያደገ ነው፤ ደኅና አድርጎ ማንበብ ይችላል። በትምህርት ቤትም ደኅና አድርጎ እየሠራ ነው። የእግዚአብሔርን ቃል በግሉ እንዴት ማንበብ እንዳለበት ሊማር ይገባዋል ብሎ አሰበ። አቶ ሰለሞን ለራሱ የሚጠቀምበትና በጣም የረዳው መጽሐፍ ቅዱስ የማንበብ ዘዴ አለው። ያንንም ዘዴ እንደገና በማጥናት ከለሳ ሊያደርግ ወሰነ።

### ዕለታዊ የጥሞና ጊዜ

መጽሐፍ ቅዱስ በማቴዎስ 4:4 እንደሚገልፀው «ሰው ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣው ቃል ሁሉ እንጂ በእንጀራ ብቻ አይኖርም» ይላል።

የጥሞና ጊዜ እንዲኖር የሚያስፈልግበት ምክንያት

1. ለመንፈሳዊ ጤንነት፤ «አሁን እንደተወለዱ ሕፃናት ተንኮል የሌለበትን የቃልን ወተት ተመኙ»፤ 1ኛ ጴጥ. 2:2፤ እንደገናም ዕብ. 5:12-14ን አንብቡ።
2. ንጹሕ ልብ እንዲኖረን ለማድረግ፤ መዝ. 118/119/:9፤ ዮሐ. 15:3። እግዚአብሔር በሕይወታችን ውስጥ ያለውን ኃጢአት ሲያሳየን፥ ልንናዘዘው ይገባናል፤ 1ኛ ዮሐ. 1:9።

3. ምክር ለማግኘት፤ 2ኛ ጢሞ. 3፡16-17፤ መዝ. 72/73/፡23-24።

4. ለመንፈሳዊ ውጊያ የሚጠቅም ብርታት ለማግኘት፤ ማቴ. 4፡1-11፤ ኤፌ. 6፡16-17።

5. እግዚአብሔርን ለመገናኘትና እርሱም ሲናገር ለመስማት፤ ዕብ. 4፡16።

## ለጥሞና ጊዜ የሚያስፈልጉዋችሁ ነገሮች

1. የተወሰነ ቦታና ጊዜ ማር. 1፡35ና ዮሐ. 18፡1።

2. የራሳችሁ የሆነ መጽሐፍ ቅዱስ።

3. በየቀኑ እግዚአብሔር የሚያስተምራችሁን ትምህርት የምትጽፉበት ማስታወሻ ደብተር።

4. እግዚአብሔር የሚያስተምራችሁን ትምህርት ለመታዘዝ ፈቃደኛ የሆነ የተከፈተና ትምህርቱን የሚቀበል ልብ።

## የጥሞና ጊዜ ደረጃዎች

1. በአጭር ጸሎት ጀምሩ። እግዚአብሔር በመንፈሱ እንዲያስተምራችሁ፤ ልባችሁን እንዲያነጻና ቃሉን ለመታዘዝ ልባችሁን የተዘጋጀ እንዲያደርግ ጠይቁት።

2. የምታነቡትን መጽሐፍ ምረጡ። የመጀመሪያውን ምዕራፍ ሦስት ጊዜ አንብቡት። በመጀመሪያ የክፍሉን አሳብ ማግኘት እንድትችሉ ቶሎ ቶሎ አንብቡት። እያንዳንዱን ጥቅስ መረዳት እንድትችሉ እንደገና አንብቡት። በመጨረሻም ለግል ሕይወታችሁ ምን እንደሚናገራችሁ ለማየት አንብቡት። ከሚቀጥለው ቀን ጀምሮ በተመሳሳይ ሁኔታ ተከታዮቹን ምዕራፎች አንብቡ።

3. ያነበባችሁትን ክፍል አውጠንጥኑት። የሚከተሉትን ጥያቄዎቻችሁን ጠይቁ።

- በዚህ ውስጥ ልታዘዘው የሚገባኝ ምን ትዕዛዝ አለ?
- ልቀበለው የሚገባኝ ምን ዓይነት አዲስ ቃል ኪዳን አለ?
- ላስወግደው ስለሚገባኝ ኃጢአት ምን ዓይነት ማስጠንቀቂያ ይሰጠኛል? ልናዘዘውና ላስተካክለው የሚገባኝ ነገር አለ?
- ስለ እግዚአብሔር፥ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ፥ ስለ መንፈስ ቅዱስ ወይም ስለ ሰይጣን የምማረው ምን አዲስ ትምህርት አለ?

4. እግዚአብሔር ለእናንተ ያስተማራችሁን ትምህርት በራሳችሁ ቃላት ጻፉ። ለግል ሕይወታችሁ የተማራችሁትን ትምህርት ለራሳችሁ አድርጋችሁ ውሰዱት። በዚያን ጊዜ ከእግዚአብሔር ለእናንተ የተሰጠ መልእክት ይሆንላችኋል።

5. ጸልዩ። እግዚአብሔር ለእናንተ የሰጠውን መልእክት ውሰዱና መልእክቱን መታዘዝ እንድትችሉ ጸልዩበት። በ4ኛው ትምህርት ውስጥ ስለ ጸሎት የተሰጡትን አሳቦች ተከተሉ።

6. የተማራችሁትን ነገር ከሌሎች ጋር ተካፈሉ። የምታካፍሉትን ነገር እራሳችሁ ታስታውሱታላችሁ።

7. እግዚአብሔር የተናገራችሁን ነገር የመታዘዝ ፍላጎት ይኑራችሁ።

አቶ ሰሎሞን የጥሞና ጊዜ መሠረታዊ ነጥቦችን እንደገና ካስታወሳቸው በኋላ ለአበራ ሁሉንም ነገረው። አበራ እንዲህ ባለ ዕቅድ መሥራት የሚችል መሆኑን ትንሽ አጠራጠረው። ነገር ግን «እሞክራለሁ» ብሎ ለአባቱ ቃል ገባለት። አቶ ሰሎሞንም «ደኅና! ማንኛውም ዓይነት ችግር ከአለብህ እኔን ጠይቀኝ። ልታካፍለኝ የምትወደው ነገር ከአለህም አካፍለኝ፤ ከምንማራቸው አዳዲስ ነገሮችም ውስጥ እርስ በእርሳችን ልንነጋገርበት እንችላለን። አንተም እንደምታውቀው እኔ የምጠቀመው በዚህ መንገድ ነው» አለው።

ብዙ ልጆች እንዲህ ባለ ዕቅድ መጠቀም ጀምረው፥ በዚሁ አድኅባቸውና ለእነርሱም ጸባያቸው ሆኖ ብርታትና ትምህርት የሚያገኙበት ታላቅ ምንጭ ሆኖላቸዋል። በእርግጥ ለልጆቻቸው የሚጠነቀቁና በዚህ መንገድም ከልጆቻቸው ጋር ለመካፈል ፈቃደኛ የሆኑ ወላጆች በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ከልጆቻቸው ጋር አብረው ያድጋሉ።

አቶ ሰሎሞን ትንንሽ ስለ ሆኑት ልጆች አሰበ። ሁልጊዜ ማታ ማታ እርሱ የሚነግራቸውን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮች ይወዳሉ። ባለቤቱም የተማሩትን ትምህርት የመታዘዝና ሥራዎች በተግባር እንዲገልጹት ትረዳቸው ነበር። አቶ ሰሎሞንም እግዚአብሔርንና ፈቃዱን እያወቁ በማደግ ላይ መሆናቸውን ተመለከተ። በአንድነት ሆነው አንዳንድ ጥቅሶችን በቃላቸው ያጠኑ ነበር፤ አንዳንድ አዝማቾችንና ደስ የሚሉ መዝሙራትን መዘመር ይወዱ ነበር። እነርሱንም ቀኑን ሙሉ ሲዘምሩ ይውሉ ነበር።

አንዳንድ ጊዜ አቶ ሰሎሞንና ቤተሰቡ በሙሉ ተሰብስቦ የሚሠራ ሥራ ይሰጣቸው ነበር። አንድ ሳምንት በየቀኑ ለአንድ ሰው የዕርዳታ ሥራ ለመሥራት ወሰኑ። በጣም አስደሳች ሳምንት ነበረ። ልጆቹ ለእናታቸው፥ ለአባታቸው እንዲሁም ለጎረቤታቸው ይሠሩ ነበር። ከቤታቸው ቀጥሎ ባለው ቤት ውስጥ ይኖር የነበረው ትንሹ ሞገስ በአጥር ውስጥ ለመሹለክ ሲሞክር አጥሩ ያዘው። ሙሉነሽ እየሮጠች ከአጥሩ አላቅቃ አባበለችው። ባደረገችው ነገር ማልቀሱን አቁሞ ወደ ቤቱ በደስታ የተመለሰው ሞገስ ብቻ አልነበረም፤ ሙሉነሽም እራሷም ተደሰተች።

ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ የይቅርታ ነገር አለ። ይህ አቶ ሰሎሞንን ስለ አበራ ካሳሰቡት ጉዳዮች አንዱ ነበር። በጣም ጥሩ ልጅ ቢሆንም ኩራተኛ ነበረ። ተሳስቶ ተሳስቻለሁ ብሎ በፍጹም አያስብም። አንድ እሑድ ማታ አበራ አስተማሪው የሰጠው የቤት ሥራ ሲሠራ እንዲያግዘው ሊጠይቅ ወደ አባቱ መጣ። ከዚያ ቀን በፊት አቶ ሰሎሞን ለአበራ የቤት ሥራውን ዓርብ ወይም ቅዳሜ ሠርቶ መጨረስ እንዳለበትና እሁድ የጌታ ቀን ስለሆነ እንዲያርፍ ነግሮት እንደነበር ሲያስታውሰው አበራ ጥቂት ምክንያቶችን አቀረበ። በመጨረሻም አቶ ሰሎሞን አበራን እሺ እረዳሃለሁ አለው። ከጥቂት ጊዜ በኋላ አበራ በጣም ደክሞት ስለነበረ አምስትንና ሦስትን እንኳ መደመር አቃተው። አቶ ሰሎሞንም ተናድዶ «በምንም ምክንያት በእሑድ ቀን የቤት ሥራ መሥራት የለብህም። ቀደም ብለህ አስበህበት በዕቅድ ልትሠራ ይገባህ ነበር። ነገ ምንም ነገር ሳትዘጋጅ ወደ ትምህርት ቤት ትሄዳለህ፤ መጥፎ ውጤትም ታገኛለህ። በል አሁን ሂድና ተኛ» ብሎ ተቆጣው።

አበራ አኩርፎ ዓይኑ ዕንባ አቅርሮ ወደ መኝታው ሄደ። ከዚህ የተነሣ እግዚአብሔር አቶ ሰሎሞንን ወቀሰው። ከመንፈስ ፍሬዎች አንዱ ራስን መግዛት ነው። አቶ ሰሎሞን ራሱን እንዳልገዛ ወይም ለልጁም ፍቅር ወይም ቸርነት እንዳላሳየው በማስተዋል ወደ አበራ መኝታ

ክፍል ሄደ። «አበራ አንተን እንደዚያ አድርጌ መናገሬ ትክክል አልነበረም እየተቆጣሁ መናገሬም ስሕተት ነበረ። ልጄ ይቅርታ አድርግልኝ» ብሎ ይቅርታ ጠየቀው።

አበራ ተገረመ። ከዚህ ቀደም አባቱ እንደዚህ ባለ ሁኔታ ተናግሮት አያውቅም። እርሱም ቀስ አለና፡- «በእርግጥ አባዬ ከዚህ ቀደም እንደ ነገርከኝ የቤት ሥራዬን ሠርቼ ቢሆን ኖሮ አንተም ባልተቆጣህ ነበር። እኔም ስለ ተሳሳትኩ፥ ይቅርታ አድርግልኝ» አለው።

አቶ ሰሎሞን ከዚህ አንዳንድ ነገሮችን ተማረ። ይህን ያደረገው ምሳሌ ለመሆን ብሎ አልነበረም፤ ይቅርታ የጠየቀው እግዚአብሔር በልቡ ስለተናገረው ነበር። ነገር ግን ከልጁ ጋር ነገሩን ለማስተካከል በትሕትና ስለቀረበ፥ ልጁን ደግሞ የተሳሳተ ነገርን በማስተካከል እርካታና ደስታ እንደሚገኝ ዐወቀ። ለልጄ ምሳሌ መሆን እንደሚገባኝ ለመማር አሥራ ሁለት ዓመታት ፈጀብኝ፤ ልጄ ግን ከዚያ ምሳሌ ለመማር የወሰደበት ጊዜ አሥራ ሁለት ሴኮንዶች ብቻ ነው» ብሎ አሰበ።

የእግዚአብሔር ቃል በማንበብና በጸሎት መጽናት ዘለዓለማዊ የሆነ ፍሬ ይሰጣል። አቶ ሰሎሞን ልጆቹን በእግዚአብሔር ቃል በማሠልጠኑ በልጆቹ ውስጥ ለውጦች እንዳሉ ተመለከተ። የእግዚአብሔር ቃል ሕያው ነው፥ በልብ ውስጥም የሚሠራ ነው።



# ክፍል 2 - ትምህርት 6

## በቤተ ክርስቲያን የአምልኮ ጊዜ አዘውትሮ የመገኘትና የመጋቢነት ልማድ

ዓላማ:- ልጆቻችሁን ዘወትር ወደ እግዚአብሔር ቤት እንዲሄዱና ጌታ በሚያበለጽጋቸው መጠን ለቤተ ክርስቲያን እንዲሰጡ ማስተማር።

በቃል የሚጠና ጥቅስ:- «ወደ እግዚአብሔር ቤት እንሂድ ባሉኝ ጊዜ ደስ አለኝ።» መዝ. 121/122/:1

መግቢያ:- ዳዊት አባቱን «አባዬ! በጠዋት መነሣትና አንተን ማየት ደስ ይላል! መጀመሪያ ትታጠባለህ፥ ቀጥሎ ጺምህን ትላጭና ጸጉርህን ታበጥራለህ! ከዚያ ቀጥሎ እማዬ ቁርስህን እንድትበላ ትጠራሃለች። ቁርስህን ከበላህ በኋላ አፍህን ትጉመጠመጥና፥ እኔን ስመኸኝ ደኅና ዋል ካልከኝ በኋላ ወደ ሥራ ትሄዳለህ» አለው።

አቶ ሰሎሞንም ሳቅ አለና «ትክክል ነህ መሰለኝ! እኔ እንደዚያ ሳደርግ ጭራሽ አላስበውም! ልማድ ሆኖብኛል» አለው።

ልማድ ማለት ይሄ ነው! የአኗኗራችን መንገድ እስኪሆን ድረስ እየደጋገምን የምንሠራው ነገር ልማድ ይባላል። የዳዊት አባት እንዳለው፥ ጥሩ ዓይነት ልማዶች አሉ። ደግሞም ጤንታችንን የሚጎዱ በቤተ ሰባችንና በጓደኞቻችን ላይ ጉዳት እንድናስከትል የሚያደርጉ እንደ ጠጪነት፥ ትምባሆ አጪያሽነትና ከሚገባ በላይ አባካኝ የሚያደርጉ ሌሎች ልማዶች አሉ።

ለክርስትና ሕይወታችን የሚረዱን ልማዶች አሉ። ስለ ጸሎት ተነጋግረናል። ልማድ ስለ ሆነብን ብቻ አንጸልይም። ሰማያዊ አባታችን ከሆነው ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገር ስለምንፈልግ እንጸልያለን። ቢሆንም እንዳንጸልይ የሚያደርጉን ብዙ ሥራዎች ይኖሩብን ይሆናል! ዘወትር ሳናቋርጥ መጸለይ እንድንችል ጊዜ የመውሰድ ልማድ እንዲኖረን ያስፈልጋል። እንዲህ ያለው ልማድ የማይኖረን ከሆነ ለክርስቶስ ክብር ለመኖር የሚያስችለንን መመሪያና ብርታት አይኖረንም።

ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ማንበብ ልማድ ተነጋግረናል። በየቀኑ መጽሐፍ ቅዱሳችሁን የምታነቡበት መደበኛ ጊዜ እንዲኖራችሁ የተወሰነ እቅድ ከሌላችሁ ቀናት እያለፉ ሲሄዱ እናንተ ግን አንድ ቃል እንኳ ሳታነቡ ትቀራላችሁ። በጠዋት መነሣት አለበለዚያም በቀኑ ውስጥ የሚመቻችሁን ሌላ ጊዜ መወሰን ይኖርባችኋል። ከፍላጎታችሁ ጋር የሚስማማውን በይበልጥ እናንተ ታውቃላችሁ። እንዲሁም ቢኖራችሁ ለእናንተ ጥሩ የሆኑ ሌሎች ልማዶች አሉ።

በእግዚአብሔር ቤት ዘወትር የመገኘት ልማድ

እሑድ ጥዋት በሳምንቱ ውስጥ ካሉት ቀናት ሁሉ የተለየ ነው። በአንዳንድ ቤቶች ውስጥ ከፍተኛ ትርምስምስ አለ። ሁሉም ሰው ተኝቶ ያረፍዳል። ከዚያ በኋላ ደግሞ ሁሉም ሰው ቤተ ክርስቲያን ለመሄድ ይዘጋጃል። አንዱ የሚያደርገውን ጫማ ያጣል። ሌላው ደግሞ የሚለብሰው ንጹሕ ልብስ ያጣል። አንዱ ደግሞ የሚረዳው ስለማያገኝ ያለቅሳል። በዚህ ጊዜ አባትና እናት መጪነቅ ይጀምራሉ፥ ቤተ ክርስቲያን እንሂድ እንሂድ እያሉ ማውጣት ማውረድ ይጀምራሉ። በመጨረሻም ለመሄድ ዝግጅታቸውን ከጨረሱ በኋላ ጉዞአቸውን ወደ ቤተ ክርስቲያን

ያመራሉ፥ ፕሮግራሙ ከተጀመረ አንድ ሰዓት ካለፈ በኋላ ይደርሱና ስብከቱ ተጋምሶ ቤተ ክርስቲያን ይገባሉ።

ለዚህ ዓይነት ትርምስምስ ጥሩ መፍትሔ የሚሆነው አስቀድሞ ዕቅድ ማውጣት ነው። የአበራ እናት ወይዘሮ ሣራ ለእናንተም የሚጠቅሙ አንዳንድ አሳቦች አሉአት። እሑድ ምን መመገብ እንዳለባቸው አስቀድማ በሳምንቱ ውስጥ ታቅዳለች። ከዝግጅቱ አብዛኛው የሚከናወነው ቅዳሜ ነው። የቤተ ሰቡን ጫማ በሙሉ አጽድቶ እንዲያዘጋጅ አበራን ታዘዋለች። ቅዳሜ ማታ እያንዳንዱ ልጅ የሚለብሰውን ልብስ በሙሉ ታዘጋጃለች። ለሙሉነሽ ቀሚሷን፥ ካልሲዎችዋን፥ ጫማዎችዋንና ንጹሕ የውስጥ ልብሷን፤ ለዳዊት ሙታንታውን፥ ሸሚዙን፥ ካልሲዎቹን እና ጫማዎቹን ታዘጋጃለች። የሕፃኑን የተስፋዬን ልብሶች አዘጋጅታ በጠረጴዛ ላይ ታስቀምጣለች። አበራ የራሱን ልብሶች እራሱ ማዘጋጀት ይችላል። ሸሚዙ ንጹሕ እንዲሆን ትቆጣጠረዋለች።

ስለዚህ እሑድ ጠዋት ሁሉም ለመዘጋጀት የሚፈጅባቸው ጊዜ በጣም ትንሽ ነው። ከዚያ በኋላ ሁሉም ቁርሳቸውን ለመብላት ይቀመጣሉ። አቶ ሰሎሞን እግዚአብሔር ያቀረበላቸውን ምግብና የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት እንዲባርክ ጸሎት ያደርጋል። ምግባቸውን እየበሉ ሳሉ የሚሄዱት ወደ እግዚአብሔር ቤት መሆኑንና እዚያ በጸጥታ መቀመጥና ማዳመጥ እንዳለባቸው ይነግራቸዋል። በቤተ ክርስቲያናቸው ውስጥ የተለያየ ዕድሜ ላላቸው ሰዎች በየዕድሜ ክልላቸው የተዘጋጀ የሰንበት ትምህርት ክፍል አለ። ስለዚህ ዋናው የእሑድ ስብሰባ ከመጀመሩ በፊት ባለው ጊዜ ውስጥ ሁሉም በዕድሜ እኩዮቻቸው ከሆኑት ከሌሎች ጋር ለመማር እኩዮቻቸው ወደ አሉበት ክፍል ይገባሉ።

ከሰንበት ትምህርት በኋላ ሁሉም ይገናኛሉ። አቶ ሰሎሞንና ወ/ሮ ሣራ በዋናው ስብሰባ ጊዜ ልጆቻቸውን መጠበቅ ያለባቸው እራሳቸው እንጂ ሌላ ሰው የእነርሱን ልጆች መጠበቅ እንደሌለበት ተስማምተዋል። አቶ ሰሎሞን አበራንና ዳዊት ይዞ ሲሄድ እሷ ደግሞ ሙሉነሽንና ሕፃኑን ተስፋዬን ይዛ ትገባለች። ወይዘሮ ሣራ ተስፋዬ ደስ እንዲለው ትንሽ ቁራሽ ዳቦና ድምጽ የሌለው መጫወቻ ይዛለት ትመጣለች። ልጆችዋ የቤተ ክርስቲያኑን ፕሮግራም መስማት የሚፈልጉትን ሰዎች እንዳይረብሹ ከኋላ በኩል ትቀመጣለች። ብዙውን ጊዜ ተስፋዬ በጥሩ ሁኔታ በጸጥታ ይቀመጣል፤ በሚያለቅስበት ጊዜ ግን ይዛው ትወጣለች። ጥሩ ቁርስ በመብላቱና እናቱ አጠገቡ በመኖሯ ደስ ስለሚለው አብዛኛውን ጊዜ ፕሮግራሙ ተጀምሮ እስኪያልቅ ይተኛል።

እግዚአብሔር አዘውትረን በቤቱ እንድንገኝ ማበረታቻ ሰጥቶናል። ዕብራውያን ምዕራፍ አሥር ከቁጥር ሃያ ሦስት ጀምሮ እስከ ሃያ አምስት «የተስፋን ቃል የሰጠው የታመነ ነውና እንዳይነቃነቅ የተስፋችንን ምስክርነት እንጠብቅ፥ ለፍቅርና ለመልካም ሥራ እንድንነቃቃ እርስ በእርሳችን እንተያይ፥ በአንዳንዶችም ዘንድ ልማድ እንደሆነው፥ መሰብሰባችንን አንተው እርስ በእርሳችን እንመካከር እንጂ፤ ይልቁንም ቀኑ ሲቀርብ እያያችሁ አብልጣችሁ ይህን አድርጉ» ይላል። አብረን መሰብሰብ ያለብን ለምን እንደሆነ የሚገልጹ ሁለት ምክንያቶች አሉ። የመጀመሪያው በእምነታችን እንድንነቃቃ፥ እምነታችንንም አጥብቀን እንድንይዝ ነው። ሁለተኛው ለፍቅርና ለመልካም ሥራ እንድንነሣሣ ነው። የጌታ መመለስ በቅርቡ ስለሚሆን ይህንን በቶሎ ማድረግ አለብን።

አንዳንድ ሰዎች ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚሄዱት ለራሳቸው ትምህርት ለማግኘት ሲሉ ብቻ ነው። ቤተ ክርስቲያን የመሄድም አንዱ ምክንያት ይሄ ነው። ቢሆንም ለሌሎችም ደግሞ በረከትና አበረታች ልንሆን ይገባናል።

## አዘውትሮ የመስጠት ልማድ

በብሉይ ኪዳን ውስጥ ሰው ካለው ነገር ሁሉ አንድ አሥረኛው የጌታ እንደሆነ የሚገልጽ ትምህርት ተሰጥቷል። ይህም አሥራት ተብሎ ይጠራል። የእግዚአብሔር ሕዝብ አሥራታቸውን ወደ ቤተ መቅደስ ማምጣት ነበረባቸው። እነርሱም አንዳንድ ጊዜ መስጠት ከሚገባቸው አሥራት በላይ መባ ያቀርቡ ነበር። ይህም አሥራትና መባ ለካህናትና ለሌዋውያን ቀለብ፥ ለቤተ መቅደሱም ለሚያስፈልጉት ነገሮች ወጪ ይሆን ነበር።

በአዲስ ኪዳን ውስጥ አሥራት እንድንሰጥ የተነገረን ልዩ ትእዛዝ የለም። ቢሆንም እንዴት መስጠት እንዳለብን የሚገልጽ ትምህርት ተሰጥቶናል። ጳውሎስ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች በጻፈው በመጀመሪያው መልእክቱ በምዕራፍ አሥራ ስድስት ቁጥር ሁለት ላይ «ከእናንተ እያንዳንዱ በየሳምንቱ በፊተኛው ቀን እንደቀናው መጠን እያስቀረ በቤቱ ያስቀምጥ» ይላል። ስለዚህ እግዚአብሔር በሳምንቱ ውስጥ ምን ያህል እንደሰጠን አስበን በዚያው መጠን የመስጠት ልምድ እንዲኖረን ያስፈልጋል። በ2ኛ ቆሮ. 8፡1-5 ውስጥ በልግስና ስለ ሰጡት የመቄዶንያ አብያተ ክርስቲያን ይናገራል። የእነርሱ በልግስና የመስጠት ምስጢር ያለው ራሳቸውን ለጌታ በመስጠታቸው ላይ ነው። ከዚህ የተነሣም ያላቸውን ሰጡ። ጳውሎስ በ 2ኛ ቆሮ. 9፡6-8 ውስጥ «በጥቂት የሚዘራ በጥቂት ደግሞ ያጭዳል፥ በበረከትም የሚዘራ በበረከት ደግሞ ያጭዳል። እግዚአብሔር በደስታ የሚሰጠውን ይወዳልና እያንዳንዱ በልቡ እንዳሰበ ይስጥ፥ በኃዘን ወይም በግድ አይደለም። እግዚአብሔር ሁል ጊዜ በነገር ሁሉ ብቃትን ሁሉ አግኝታችሁ ለበጎ ሥራ ሁሉ ትበዙ ዘንድ፥ ጸጋን ሁሉ ሊያበዛላችሁ ይችላል» ይላል።

ልጆቻችሁ ይህ ልማድ እንዲኖራቸው እንዴት ልታስተምሯቸው ትችላላችሁ? ከሁሉ በመጀመሪያ በሳምንቱ ውስጥ እግዚአብሔር እናንተን በአበለጸገበት መጠን መስጠትን ማዘውተር አለባችሁ። ልጃችሁም መባ በሚሰበሰብበት ወቅት ገንዘቡን በመሰብሰቢያው ዕቃ ውስጥ እንዲያስቀምጥ አድርጉት። በዚያ መንገድ መስጠትን ሊማር ይችላል። ልጃችሁ ገንዘብ የሚያገኝበት የገቢ ምንጭ ቢኖረው ካገኘው ገቢ አንድ አሥረኛውን ቢሰጥ ለጌታ ጠቃሚ የሆነውን ይህን አገልግሎት መስጠት እንዲጀምር ሊረዳው ይችላል።

አንድን ልጅ የሚያዘወትረውን ጸባይ ለማስተማር ራስም ያንኑ ሥነ ሥርዓት አክባሪ ሆኖ መገኘት ያስፈልጋል። ጠቃሚ በሆኑት በእነዚህ ሥነ ሥርዓቶች አንጻር እራስችንም ሥነ ሥርዓት አክባሪ ሆነን ብንገኝ፥ ልጆቻችንም እኛን ይከተላሉ። ልክ እንደ አባታቸው ወይም እንደ እናታቸው ለመሆን ይፈልጋሉ። መጽሐፍ ቅዱስ በሚልክያስ 3፡10 ውስጥ «በቤቴ ውስጥ መብል እንዲሆን አሥራቱን ሁሉ ወደ ጎተራ አግቡ፤ የሰማይንም መስኮት ባልከፍትላችሁ በረከትንም አትረፍርፌ ባላፈስላችሁ፥ በዚህ ፈትኑኝ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር» ይላል እስከ ልጆቻችንን በሕይወት ዘመናቸው ሁሉ የሚጠቅሙአቸው ባህርያትን እንዲመሠርቱ እያደረግን እንምራቸው። ልጆች የበሰሉ ሆነው እንዲያድጉ በእግዚአብሔር ቤት ሳያቋርጡ አዘውትሮ በመገኘት ከእግዚአብሔር ጋር መተባበር ያስፈልጋቸዋል። ለእግዚአብሔር ያላቸውን ፍቅር እንዲገልጹና ለሚያደርግላቸው ነገር እንዲያመሰግኑት፥ እግዚአብሔር ለእነርሱ ከሰጣቸው ውስጥ እነርሱም መልሰው እንዲሰጡት መስጠትን አስተምሯቸው።



# ክፍል 3

# ትምህርት 7-13

## ልጆች መልካም ጸባይ እንዲኖራቸው ማሠልጠን

የክፍሉ ዓላማ:- ወላጆች ልጆቻቸውን የሚያሳድጉበት በእግዚአብሔር ቃል ላይ የተመሠረተ ጽኑ ዓላማ እንዲኖራቸው ማድረግ።

የክፍሉ ጥቅስ:- «እግዚአብሔር አለ፥ አብርሃም ጽድቅንና ፍርድን በማድረግ የእግዚአብሔርን መንገድ ይጠብቅ ዘንድ ልጆቹንና ከእርሱ በኋላ ቤቱን እንዲያዝ አውቃለሁና» ዘፍ. 18:19።

## ክፍል 3 - ትምህርት 7

### ሥነ ሥርዓት

ዓላማ:- ወላጆች ልጆቻቸው ብስለት ያላቸውና ጽኑ የሆኑ የክርስቶስ ተከታዮች አድርገው እንዲያሳድጓቸው በእምነት ገንቢ የሆነ ሥነ ሥርዓትን እንዲከተሉ ለማበረታታት።

በቃል የሚጠና ጥቅስ:- «ነገር ግን ለሌሎች ከሰበክሁ በኋላ ራሴ የተጣልሁ እንዳልሆን ሥጋዬን እየጎሰምሁ አስገዛዋለሁ።» 1ኛ ቆሮ. 9:27

መግቢያ:- የወንጀለኛነት ጸባይ መነሻ ምን እንደሆነ ለማወቅ የተደረገው የስታቲስቲክስ ጥናት እንደሚያሳየው «ወንጀለኞች በቤት ውስጥ ያደጉ ናቸው።» አብዛኛው አሰቃቂ ወንጀል የሚፈጸመው በቤታቸው ከወላጆቻቸው ምንም ዓይነት ቁጥጥር የማይደረግባቸውና ሥነ ሥርዓት የጎደላቸው ወጣቶች ናቸው። ብዙ ወላጆች ልጆቻቸው ለሚፈጽሙት ተግባር ያላቸውን ኃላፊነት ከምንም አይቆጥሩትም፥ ወይም ሲያጠፉ በቸልተኝነት ያልፏቸዋል። ልጆቻቸው ሥነ ሥርዓት ያላቸውና በሚገባ የሠለጠኑ ሆነው እንዲያድጉ በቂ ጥንቃቄ አያደርጉም። አንዳንዶች ደግሞ ምን ማድረግ እንዳለባቸው ስለማያውቁ ምንም አያደርጉም።

### ሥነ ሥርዓት ምንድነው?

ሥነ ሥርዓት ልጅን በሚሄድበት መንገድ እንዲራመድ ማሠልጠን /መምራት/ ማለት ነው፤ ምሳሌ 22:6። ሥነ ሥርዓት ልጃችሁን ለመምራት ያላችሁ ልዩ መብት ከመሆኑም በላይ ልጃችሁ እንዴት መኖር እንዳለበት ለማስተማር የምታደርጉለትን ዕርዳታ ሁሉ ይጨምራል።

ይህ የማሠልጠን ተግባር ልጁን ያስተካክለዋል፥ ያንጸዋል፥ ያበረታዋል ደግሞም ትክክኛ ያደርገዋል። ስለዚህ ቅጣት የሚያስፈልግበት ጊዜ ይኖራል ማለት ነው። ሥነ ሥርዓት ልጅ እስኪያድግና የራሱ የሆነ ሥነ ሥርዓት መለማመድ ወይም መከተል እስኪጀምር ትክክለኛ ጠባይ በሥራ ላይ እንዲውል በማድረግ መጠበቅ አለበት። ማበረታታትም የሚያስፈልግበት ቦታ አለ። ማስተማርም የሚያስፈልግበት ቦታ አለ።

ሥነ ሥርዓት ክርክር ባለመፍጠር በቤት ውስጥ እንደ መሥራት የት/ቤት ሰዓት ማክበርንና የቤት ሥራን መሥራት ያሉትን ተግባራት ማስተማርንም ይጨምራል።

ከዚህም አልፎ ልጅ በሕይወቱ ዘመን የሚገጥሙትን ችግሮች በልበሙሉነት በተስፋ፥ በጉጉትና በቆራጥነት መቋቋም እንዳለበት ማስተማርንም ይጨምራል። ልጃችሁን ወደ ተትረፈረፈ ሕይወት እንድትመሩት የሚያስችላችሁ ልዩ ዕድል ነው። ይህን ሁሉ ለማድረግ ወደ ሃያ ዓመት ይፈጃል።

## ሥነ ሥርዓትን ማስተማር ያለበት ማን ነው?

እግዚአብሔር ይህን ኃላፊነት ለአባቶችና ለእናቶች ሰጥቶአል፤ ኤፌ. 6፡1-4። ሁለቱም ወላጆች ለልጆቻቸው ተጠያቂ ናቸው። ልጆች ከእግዚአብሔር ለወላጆች በኃላፊነት የተሰጡ ናቸው። ወላጆችም የእግዚአብሔር ስጦታ እንደሆኑ ተቀብለው ለእርሱ ክብር ማሳደግ አለባቸው። አባት የማስተማሩንና የማሠልጠኑን ሥራ በመሪነት ደረጃ ይወስዳል። እናት በዕለታዊ ሕይወት የሚኖርቱን ኑሮ በተግባር እንዲገልጽ ለማድረግ ብዙ የመምራት ኃላፊነት አለባት። ይህም ወላጆች ስለ ሥነ ሥርዓት ያላቸው ዓላማ በአንድነት ዕቅድ ማውጣትና መወያየት ምን ያህል ጠቃሚ እንደሆነ ያመለክታል። ለምሳሌ ይህን መጽሐፍ እንደ መመሪያችሁ አድርጋችሁ ልትጠቀሙበት ትወስኑ ይሆናል። ስለዚህ ሁለታችሁም አንብባችሁት ልጆቻችሁን ለምታሠለጥኑበት ዓላማዎች አብራችሁ ዐቅዱ፤ እንደዚህ ካደረጋችሁ ሁለታችሁም ለተመሳሳይ ግብ ትሠራላችሁ ማለት ነው።

## ሥነ ሥርዓትን ማስተማር ያለባችሁ መቼ ነው?

መልሱ «ሁልጊዜ» ነው። ሥነ ሥርዓትን ማስተማር እራሱ የማሠልጠን ሥራ ከሆነ፥ መጀመር ያለባችሁ ከተወለደበት ጊዜ ጀምሮ ሲሆን፥ ከእናንተ ነፃ እስከሆነና የራሱን ኑሮ እስከ መሠረተ ድረስ መቀጠል አለባችሁ። ምናልባት ለመጀመር ትፈሩ ይሆናል። 2ኛ ጢሞ. 1፡7 «እግዚአብሔር የኃይልና የፍቅር ራስንም የመግዛት መንፈስ እንጂ የፍርሃት መንፈስ አልሰጠንም» ይላል። በዚህ ጥቅስ ውስጥ ፍርሃት የበታችነት ስሜት ወይም ብቁ አለመሆን ማለት ነው። እግዚአብሔር ለሥራው የማትበቁ አድርጎ አልፈጠራችሁም። ልጆችን ሰጥቶአችኋል፥ እንዲሁም የኃልና የፍቅር መንፈስ ከመልካም አእምሮ ጋር ይሰጣችኋል። እግዚአብሔርን እንዲመራችሁ ጠይቁት። ለእያንዳንዱ ልጅ ኃላፊነት እንዲሰማችሁ የሚያደርግ ፍቅር እንዲሰጣችሁ ጠይቁት። ለክብሩ ጸንተው የሚቆሙ እንዲሆኑ አድርጋችሁ እንድታሠለጥኑአቸውና እንድትመሩአቸው የሚያስችል ጥበብ እንዲሰጣችሁ ጠይቁት።

## ሥነ ሥርዓትን እንዴት አድርጋችሁ እንደምታስተምሩ

ልጆቻችሁ የሚኖሩትን ኑሮ በየትኛውም አቅጣጫ ቢሆን ለመከታተል ዝንባሌ ያላችሁና ጥንቁቆች ሁኑ። ለጥያቄዎቻቸው መልስ ለመስጠት፥ የሚናገሩትን ሁሉ ለመስማትና በሚገባ እነርሱን ለመርዳት ዝግጁ ሁኑ። ኑሮ ለልጆቻችሁ በእንቆቅልሽና ውስብስብ በሆነ ነገር የተሞላ ነው። ወደ ኋላ መለስ ብላችሁ የራሳችሁን የልጅነት ጊዜና በዚያን ጊዜ ግራ ያጋቡአችሁ የነበሩትን ብዙ ነገሮች አስታውሱ። እንደዚህ ያሉትንም ነገሮች ለልጆቻችሁ ግለጹላቸው።

አስፈላጊ ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ ልጃችሁን ለመቅጣት አትፍሩ። የእግዚአብሔር ቃል በመጽሐፈ ምሳሌ 13፡24፦«በበትር ከመምታት የሚራራ ሰው ልጁን ይጠላል፤ ልጁን የሚወድ ግን ተግቶ ይገሥጸዋል» በማለት ያረጋግጥላችኋል። ሕፃናት በሚያጠፉበት ጊዜ

ወዲያውኑ ቅጣት ሊሰጣቸው ያስፈልጋል። ያን ጊዜ ጥፋት ሲያጠፉ እንደሚያስቀጣቸው ይረዳሉ።

ልጆቻችሁ ብዙ ፍቅርና ማንነታቸውን የምትረዱበት ማስተዋል ያስፈልጋችኋል። ፍቅር ሰብዓዊ አቋም ያሳድጋል። በፍቅር የጸሐይ ብርሃን የልጅ ሰብዓዊ አቋም ያድጋል፤ ልክ እንደ አበባም ይፈካል። ያን ጊዜ በጸባዩ የተዝናና እርግጠኝነት የተሞላውና ሥጋት የሌለበት ይሆናል።

እንዲሁም ደግሞ በሥነ ሥርዓት እንዲታነጽ ልጃችሁ መልካም የሆነ ቁጥጥር ያስፈልገዋል። ቁጥጥር ልጃችሁ በሕይወቱ ዘመን ችግር በገጠመው ጊዜ ሊረዳው የሚችል መልካም ሥነ ምግባርን ይቀርጽለታል።

ሥነ ሥርዓት በጎደለው ፍቅር ያደገ ልጅ ጸባዩ ብልሹ ይሆናል፤ ፍቅር በጎደለው ሥነ ሥርዓት ያደገ ልጅ ደግሞ የተጣመመ የተፈጥሮ ጸባይ ይኖረዋል ብለን መናገር እንችላለን።

ስለዚህ እያንዳንዱን ልጅ እንዴት አድርገን ማሳደግ እንዳለብን በማወቅ በኩል ምሪትን እንዲሰጠን ዘወትር ሳናቋርጥ ጌታን መጠየቅ አለብን። እያንዳንዱ ልጅ ከሌላው የተለየ ነው። እኛ ለምናስተምራቸው ሥነ ሥርዓት እያንዳንዱ ልጅ ከሌላው የተለየ ነው። እኛ ለምናስተምራቸው ሥነ ሥርዓት እያንዳንዱ የተለያየ አቀባበል አለው። የሚቀበሉት በተለያዩ መንገዶች ነው። ስለዚህ ልጆቻችን ይበልጥ ጥሩ ሆነው ያድጉ ዘንድ እንዴት መንከባከብ እንደ አለብን ለመረዳት ዝግጁና ንቁ መሆን ይኖርብናል። «እኔ አምላክህ እግዚአብሔር፥ አትፍራ፥ እረዳሃለሁ ብዬ ቀኝህን እይዛለሁና» ኢሳ. 41፡13።

በማስተማርና በማሠልጠን መሃከል ልዩነት አለ። ሃና ልጇን ለጌታ አሠለጠነችው። ሳሙኤል ሐና ... «ጌታ ሆይ ... ለባሪያህም ወንድ ልጅ ብትሰጥ ዕድሜውን ሁሉ ለጌታ እሰጠዋለሁ ...» ስትል ለጸለየችው ጸሎት ከጌታ ዘንድ መልስ ሆኖ የተሰጣት ልጅ ነበር፤ 1ኛ ሳሙ. 1፡11። ሳሙኤል ገና ልጅ ሆኖ ሳለ ወደ ሴሎ ወሰደችውና ለካህኑ ለዔሊ «ስለዚህ ሕፃን ጸለይሁ፤ እግዚአብሔርም የለመንሁትን ልመናዬን ሰጥቶኛል፤ እኔም ደግሞ ለእግዚአብሔር ሰጥቼዋለሁ፤ ዕድሜውን ሁሉ ለእግዚአብሔር የተሰጠ ይሆናል፤» ብላ አለች፤ 1ኛ ሳሙ. 1፡27-28። ሳሙኤል በቤቱ ውስጥ ከእናቱ ጋር በነበረበት ወቅት መታዘዝንና ሽማግሌዎችን ማክበር የተማረ መሆኑ በግልጽ ይታያል። ሳሙኤል ዔሊ የጠራው እየመሰለው ሦስት ጊዜ ከመኝታው እየተነሣ ወደ ዔሊ ሮጠ። ሳሙኤል በሕይወቱ ዘመን ሁሉ ሳያቋርጥ ጌታን ሲያገለግል ኖረ።

በሌላ በኩል ደግሞ ሁለቱን የዔሊን ልጆች እንመለከታለን። ሁለቱ የዔሊ ልጆች የማይታዘዙ፥ ሥነ ምግባር የጎደላቸውና ለጌታ የቀረበውን መሥዋዕት ምን ያህል ያቃልሉ እንደነበር መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል።


ዔሊ ልጆቹ ምን ይሠሩ እንደነበር ያውቃል። ትክክል የነበረውን ነገር አስተምሮአቸው ነበር። ነገር ግን በጽሑፍ እንደምናገኘው «ስለ ክፉ ሥራችሁ ከዚህ ሕዝብ ሁሉ ሰምቻለሁና ስለ ምን እንዲህ ያለ ነገር ታደርጋላችሁ? ልጆቼ ሆይ፥ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ኃጢአተኛ በማድረጋችሁ ስለ እናንተ የደረሰኝ ወሬ መልካም አይደለምና» ብሎ ይናገራል፤ 1ኛ ሳሙ. 2፡23-24።

ዔሊ ልጆቹ ሕፃናት ሳሉ በሥነ ሥርዓት ከማሠልጠን ቸል አለ፤ መጽሐፍ ቅዱስም እንደሚለው «የአባታቸውን ቃል አልሰሙም፤» 1ኛ ሳሙ. 2፡25። እግዚአብሔር የዔሊ

ልጆችና ከእነርሱ በኋላ የሚወለዱት ካህናት እንዳይሆኑ አደረገ፤ 1ኛ ሳሙ. 3፡13። «ልጆቹ የእርግማን ነገር እንዳደረጉ ዐውቆ አልከለከላቸውምና ስለ ኃጢአት በቤቱ ለዘለዓለም እንድፈርድ አስታውቄዋለሁ» ይላል። ዔሊ ልጆቹን አስተማራቸው፥ ነገር ግን በሥነ ሥርዓት አላሠለጠናቸውም፤ አልከለከላቸውም ወይም አልቀጣቸውም፤ የተናገራቸውን ነገር እንዲያደርጉ አላስገደዳቸውም ወይም እንዲታዘዙ አላደረጋቸውም።

ዔሊ ጌታን ይወድ ነበር። ቅንና የክህነቱንም ሥራ በታማኝነት የሚሠራ ሰው ነበር፤ ነገር ግን ልጆቹን አላሠለጠናቸውም፤ አላስተማራቸውም፤ ቃሉንም እንዲያከብሩ አላስገደዳቸውም። ሥነ ሥርዓት ከመታዘዝ የበለጠ እንደሆነ እናስታውስ። «ሥነ ሥርዓት ምንድነው?» የሚለውን ክፍል ተመልሳችሁ ተመልከቱና እንደገና አንብቡት።

የማሠልጠን ትምህርታችሁ በሙሉ በእግዚአብሔር ቃል ላይ የተመሠረተ መሆን አለበት። ልጃችሁን በታማኝነት ስታስተምሩትና በእግዚአብሔር ቃል መሠረታዊ እውነት ስትመሩት ወደፊት የሚያደርጋቸውን ነገሮች ሁሉ የሚገነባበት መሠረት ያገኛል። በሌላ ሰው ሕይወት ውስጥ መሠረት የመጣል ሥራችሁ ሊከናወንላችሁ የሚችለው እራሳችሁ መጽሐፍ ቅዱስን ስታጠኑና የጸሎት ጊዜ ሲኖራችሁ ነው።



## ክፍል 3 - ትምህርት 8

### መታዘዝን ለማስተማር የሚያገለግሉ መመሪያዎች

ዓላማ:- ወላጆች ልጆቻቸውን ገና ትንንሾች ሳሉ መታዘዝን ማስተማር ሊጀምሩ እንደሚችሉ ለማስገንዘብ።

በቃል የሚጠና ጥቅስ:- «ልጆች ሆይ፥ ይህ ለጌታ ደስ የሚያሰኝ ነውና፥ በሁሉ ለወላጆቻችሁ ታዘዙ።» ቆላ. 3፡20

መግቢያ:- ወይዘሮ በላይነሽ የሁለት ዓመት የሴት ልጇን ጸጉር ታበጥር ነበር። ሚሚ ማበጠሪያውን ከእጇ ነጠቀችና መሬት ላይ ወረወረችው ወይዘሮ በላይነሽ በሁኔታው መቆጣን በጣም በመደነቅ ሕፃኗን ልጅ ትኩር ብላ እየተመለከተች «ሂጂና ማበጠሪያውን አንስተሽ አምጪልኝ» አለቻት። ገና አፏን በመፍታት ላይ የነበረችው ሚሚም «እምቢ!» አለች።

እናቷም «ምን ሆነች! ልጆች ዕድሜአቸው ሁለት ዓመት በሚመላበት አካባቢ የራሳቸውን ፈቃድ ብቻ መፈጸም የሚፈልጉበት ጊዜ እንደሚመጣ ሰምቻለሁ። ይህቺም ልጅ እንደዚያ የምታደርገብት ዕድሜ ላይ ደረሰች ማለት ነውን?» ብላ አሰበች።

ብዙ ጠቃሚ ነገሮችን ልታስተምራት በምትችልበት በዚህ ጊዜ ልጇን ችል ማለት እንደሌለባት ታውቃለች። ለሁሉም ጊዜ አለው እንደሚባለው፥ ሚሚን በግድ ሳይሆን ቀስ በቀስ የራሷን ፈቃድ ለእናቷ ትእዛዝ ማስገዛት እንዳለባት የምታስተምርበት ትክክለኛው ጊዜ ይሄ መሆን አለበት። ስለዚህ «ሚሚ! ሂጂና ያን ማበጠሪያ አምጪ» ብላ እንደገና ተናገረች።

ሚሚ ወዲያው እናቷን እያየች ራስዋን በመነቅነቅ «እምቢ!» አለች። በጣም ደስ የምትል ልጅ ነበረች። ሚሚ መጥፎ ጸባይ ያላት ልጅ ሆና አልነበረም። ስለዚህ ወይዘሮ በላይነሽ ማበጠሪያውን እራሷ ሄዳ ልታመጣና ነገሩን በቀላሉ ልታሳልፈው አሰበች።

ወዲያውኑ ደግሞ ለሚሚ ሁለት ትእዛዞች እንደሰጠቻትና ሚሚ አንዱንም እንኳ እንዳልታዘዘች አሰበች። እንድትታዘዝ ካላደረገቻት ደግሞ ነገሩን እንዲያው በማሳለፏ አለመታዘዝን ታስተምራታለች።

«ሂጂና ማበጠሪያውን አምጪ» ብላ አዘዘቻት። ሚሚ ከቦታዋም አልተንቀሳቀሰችም፥ ስለዚህ እናቷ በአርጩሜ እጅዋን መታቻትና «ሂጂና አምጪ አይደለም የምልሽ!» አለቻት።

ሚሚ ፊቷ ጠቆረ፤ ማልቀስም ጀመረች፤ ቢሆንም ሄዳ ማበጠሪያውን አነሳችና ለእናቷ አምጥታ ሰጠቻት።

«አመሰግንሻለሁ ሚሚ፤ አንድ ነገር እንድታደርጊ ስጠይቅሽ ማድረግ እንዳለብሽ እንድትረጂ እፈልጋለሁ» አለቻት። ወዲያውኑ ሕፃኗን እቅፍ አደረገችና ዕንባዋን ጠርጋ ግንባርዋ ላይ ሳመቻት። ሚሚም ወደሚሞቀው ወደ እናትዋ ጉያ ሽጉጥ ብላ እናቷን ቀና ብላ እያየች ፈገግ ማለት ጀመረች።

### መታዘዝን ማስተማር

ልጆችን ማሳደግ ደረጃዎችን በመውጣት ሊመስል ይችላል። ደረጃዎችን አንድ በአንድ መውጣት በጣም የተሻለ ነው። የመጀመሪያውም ደረጃ ልጅን በግድ ሳይሆን ቀስ በቀስ ለትእዛዛችሁ እንዲገዛ ወይም እንዲታዘዛችሁ ማስተማር ነው። ይህን የመጀመሪያውን ደረጃ እንደሚገባ ካላስተማራችሁና ልጆቻችሁም ካልተማሩት ሌሎች ጥረቶች በሙሉ ከንቱ ይሆናሉ።

ልጆቻችሁ ገና ሕፃን ሳሉ መታዘዝን ማስተማር ከጀመራችሁና በየቀኑ ማስተማራችሁን ከቀጠላችሁ አስቸጋሪ አይሆንም። ልጆች በሁሉ ነገር ለወላጆቻቸው እንዲታዘዙ ትእዛዝን የሰጠው እግዚአብሔር ነው። ይህንንም እነርሱ በራሳቸው ሊማሩት አይችሉም፤ ስለዚህ እንድትረዷቸው ይፈልጋሉ። እናንተም እግዚአብሔር የነገራችሁን ነገር እንደምታደርጉ ስለምታውቁ እርግጠኞች ሆናችሁ ልታስተምሩ ትችላላችሁ። ጠቃሚ የሆነውን ይህን የመጀመሪያ ደረጃ በምታስተምሩበት ጊዜ ልትከተሉዋቸው የሚገቡ ጥቂት መምሪያዎች አሉ።

<u>ልጃችሁ እንዲታዘዝ የምትፈልጓቸውን ትእዛዛት ብቻ ስጡ።</u>

አንዳንድ ወላጆች ቀኑን ሙሉ «ያንን እንዳታደርግ!» « ያንኛውን ተው» እያሉ ልጆቻቸው ላይ ሲጮሁ ይውላሉ። ልጁ ወዲያውኑ ወላጆቹ የሚናገሩት ከልባቸው እንዳልሆነ አድርጎ ይረዳል። እናትና አባታቸው ዞር ሲሉ ልጆች እንዳያደርጉ የተከለከሉትን ነገር ደጋግመው መሥራታቸውን ይቀጥላሉ። ልጃችሁ እናንተ የምትፈልጉትን ብቻ እንዲያደርግ አስቀድማችሁ ማሰብና መጠየቅ አለባችሁ።

<u>ትእዛዝ በምትሰጡበት ጊዜ ማስፈጸም አለባችሁ።</u>

ልጃችሁ እንዲያደርግ የነገራችሁትን ነገር ወዲያውኑ ተቀብሎ የሚታዘዝ መሆኑን መከታተል የእናንተ ኃላፊነት ነው። እንዲያደርግላችሁ የፈለጋችሁትን የተረዳው መሆኑን አረጋግጡ። ከዚያ በኋላ የታዘዘውን እንዲፈጽም ተጠባበቁ። የማይታዘዛችሁ ከሆነ አመቺ የሆነ ጥቂት ቅጣት መስጠትና ትእዛዙን እንዲፈጽም ማድረግ አለባችሁ። ቅጣታችሁ እንደ ዕድሜው አመቺ የሆነና አልታዘዝም ካለበት ከጥፋቱ ጋር ተመጣጣኝ መሆን አለበት።

በቀን ውስጥ ሰፋ ያለውን ጊዜ ከልጆች ጋር የምትውለው እናት ስለሆነች ይህ በቅድሚያ ማሠልጠንን የመጀመር ተግባር በይበልጥ የሚመለከተው እናትን ነው። ስለዚህ «እናቶች፥ ልጆቻችሁ በሕፃንነት ጊዜአቸው ከነርሱ ጋር ሁኑ። ሥራ መሥራትና በገንዘብ መርዳት አስፈላጊ ሊመስል ይችላል። ነገር ግን ልጆቻችሁ ጠቃሚ ትምህርት የሚያገኙባቸው እነዚያን የሕፃንነት ጊዜአቸውን እንደገና መልሳችሁ በገንዘብ ልትገዙት አትችሉም» ብሎ መናገር ይቻላል።

እንደዚህ ዓይነትን የማሠልጠን ሥራ እንዳንሠራ ጊዜ የሚያሳጡን በቤት ውስጥ ብዙ መሠራት ያለባቸው ሥራዎች አሉብን ትሉ ይሆናል። ልጆች አንታዘዝም በሚሉበት ጊዜ ምን ያህል ጊዜና ጉልበት እንደምታባክኑ አስቡ። ትእዛዝ በግድ እንዲፈጸም በማታደርጉበት ጊዜ በቤት ውስጥ ምን ያህል ጭቅጭቅ እና አሳዛኝ ነገር እንደሚፈጠር አስቡ። ታዛዥ ልጆችን ማሳደግ በጣም የቀለለ ነው።

<u>በተቻለ መጠን ትእዛዝ አታብዙ፥ ጥቃቅን ነገሮችን ቸል በሉ።</u>

ለሕፃን የሚሰጡ ትእዛዛት በጣም ጥቂት መሆን አለባቸው። አደገኛ የሆኑ ነገሮችን ሕፃን ልጅ ከሚደርስበት ሥፍራ አርቃችሁ አስቀምጡ። ጀማሪውን ሕፃን ልጅ ተስፋ አታስቆርጡት።

የታዘዘውን ነገር በሚገባ ሠርቶ ሲጨርስ በትክክል እንደሠራ ንገሩት። ፈገግታችሁና የሠራውን ሥራ መቀበላችሁ ለእርሱ ብዙ ጥቅም አለው።

## ፍርዳችሁ የተስተካከለና ብስለት ያለው ይሁን።

ከዓላማችሁ አንዱ መታዘዝን ማስተማር ከሆነ፥ /ያም እንደ ክርስቲያናዊ ቤተሰብ መሆን አለበት/ ይህን የተወሰነ ዓላማ መያዛችሁ ከሌሎች ነገሮች ጠቃሚ የሆኑትን ነገሮች ለይቶ ለማውጣት የሚረዳችሁ ሆኖ ታገኙታላችሁ።

ለምሳሌ አንድ ልጅ እናቱ ላይ ሊታቀፍ ፈለገ። ጫማው በጣም ቆሽሾ ስለነበረ፥ በሚታቀፍበት ጊዜ የእናቱን ቀሚስ በጭቃ ረግጦ አበላሸባት። በዚህን ጊዜ እርስዋ በጣም ትናደድና በጥፊ መትታው ከእቅፍዋ ላይ ገፍታ ካወረደችው በኋላ እርሱ እያለቀሰ ወደ ውጭ ወጣ። በሌላ ጊዜ ልጁ ሆን ብሎ አልታዘዝም ሲላት ጓደኛውን ትጠቅስና ልጁ ከወጣ በኋላ ሁለቱም ይሳሳቃሉ። የመጀመሪያው ጥፋት ለእናትየዋ ተጨማሪ ሥራ ሰጥቷታል፥ ምንም እንኳን ልጁ ዐውቆ ባያደርገውም እርሷን አናድዷታል። ያጠፋውን ጥፋት አሳይታ ልታልፈው ትችል ነበር። በሁለተኛው ደረጃ ግን አልታዘዝም ባለበት ጊዜ እናቱ እንዲታዘዛት ማድረግ ነበረባት፥ በተጨማሪም ቅጣት መስጠት አስፈላጊ ነበር።

## ልጃችሁ ሊያደርገው የምትፈልጉትን ነገር ቀደም ብላችሁ ንገሩት።

ልጆቻችሁን ስታዝዙ በማሰብና በማስተዋል መሆን አለበት። እነርሱም ደግሞ በዚያው መንገድ ትእዛዙን ይፈጽማሉ።

ለምሳሌ ልጆች ደስ ብሎአቸው እየፈነደቁ በግቢው ውስጥ ይጫወቱ ይሆናል። እርስዎም ግዋ ወደ ሱቅ ሄዶ ሳሙና እንዲገዛለዎት ይፈልጋሉ። ስለዚህ ወጣ ብለው በጥዋና «ማሞ! በ10 ደቂቃ ውስጥ ሄደህ ከሱቅ ሳሙና እንድትገዛልኝ እፈልጋለሁ። ቶሎ ጨዋታህን ጨርስና ሄደህ ግዛልኝ» ብለው ይንገሩት። በዚህ መንገድ ልጁ ስለ መልእክቱ ለማሰብ ጊዜ ይኖረዋልና ደስ እያለው እየሮጠ ወደ ሱቅ ሊሄድላችሁ ይችላል። እርስዎ ትእዛዙዎን ከረር በማድረግ:- «ማሞ ና ይህን ገንዘብ ውሰድና ከሱቅ ሳሙና ግዛልኝ። ቶሎ! ፈጠን በል! አሁን እፈልገዋለሁ» ብለው ሊያስገድዱት ይችሉ ነበር።

በዚህ ጊዜ እርሱ ደስ እንዲለው እንደማትፈልጉ ሊሰማው ይችላል። ሁልጊዜ ለእናንተ እንዲሠራ ብቻ እንደምትፈልጉት አድርጎ ይቆጥረዋል። ልጆች የሚሠሩበት ጊዜ እንደሚያስፈልጋቸው ሁሉ የሚጫወቱበትም ጊዜ ያስፈልጋቸዋል።

መታዘዝን ለማስተማር ስትፈልጉ እነዚህን መመሪያዎች በአእምሮአችሁ ብትይዙ የተወሰነ የማስተማሪያ አሳብ እንዲኖራችሁ ቀለል ያለ መንገድ የሚፈጥሩላችሁ ከመሆናቸውም በላይ ልጆቻችሁም እነርሱ ምን እንዲያደርጉ እንደምትፈልጉ በቀላሉ ሊረዱ ይችላሉ። የተወሰነ ዓላማን የመከተልን ጠቃሚነት ማየት እንድትችሉ እንዲረዳችሁና በተጨማሪም ደግሞ በዚሁ ዓላማችሁ መትጋት እንድትችሉ ብርታት እንዲሰጣችሁ እግዚአብሔርን ጠይቁት።



## ክፍል 3 - ትምህርት 9

## ልጆች እንዲታዘዙ ማድረግ

ዓላማ:- ትእዛዝ ወዲያው እንዲፈጽሙ ለልጆቻቸው በትጋት እንዲያስተምሩአቸው ለወላጆች መመሪያ ለመስጠት።

በቃል የሚጠና ጥቅስ:- /ሳሙኤል/ ወደ ዔሊ ሮጠ «እነሆኝ የጠራኸኝ» አለው። 1ኛ ሳሙ. 3:5

መግቢያ:- በእርግጥ ልጆቻችን እንዲታዘዙን እንፈልጋለን፤ ነገር ግን እንዴት አድርገን እንዲታዘዙ ልናደርጋቸው እንችላለን? እግዚአብሔር መልሱን በቃሉ ሰጥቶናል። ምሳሌ 22:15:- ስንፍና በሕፃን ልብ ታስሮአል፤ የተግሣጽ በትር ግን ከእርሱ ያርቃታል።

«ቆይ እስኪ! ልጆቻችንን በበትር መቅጣት አለብን ማለቱ ነውን? ልጄን ልጎዳው አልፈልግም። ያንን እንዳላደርግ ልጄን በጣም እወደዋለሁ» ትሉ ይሆናል። እግዚአብሔር «በበትር ከመምታት የሚራራ ሰው ልጁን ይጠላል፤ ልጁን የሚወድ ግን ተግቶ ይገሥጸዋል» ይላል፤ ምሳ. 13:24። «ሕፃንን ከመቅጣት ቸል አትበል . . . በበትር ትመታዋለህ ነፍሱንም ትታደጋለህ፤» ምሳ. 23:13-14።

«ልጄ ምንም ተጽእኖ ሳይኖርበት በነፃነት እንዲያድግ እፈልጋለሁ» ትሉ ይሆናል። እግዚአብሔር ግን «በትርና ተግሣጽ ጥበብን ይሰጣሉ፤ ያልተቀጣ ብላቴና ግን እናቱን ያሳዝናል» ይላል፤ ምሳ. 29:15። ደግሞ «በጥቃቅን ነገሮች አለመታዘዝ ይህን ያህል ትልቅ ነገር አይደለም። ገና ሕፃን ልጅ ነው፤ እስኪያድግ ከእርሱም ጋር በደምብ መግባባት እስክችልና እርሱም ይበልጥ መረዳት እስኪችል ድረስ እጠብቀዋለሁ» ብላችሁ ታስቡ ይሆናል። የእግዚአብሔር ቃል ግን:- «ተስፋ ገና ሳለች ልጅህን ገሥጽ፥ መሞቱንም አትሻ» ይላል፤ ምሳ. 19:18።

«በዚህ መንገድ ሥነ ሥርዓትን ባስተምረው ይበልጥ ዐመጸኛ ልጅ ይሆናል። ስለዚህ እንዴት ላደርግ?» ብላችሁ ታስቡ ይሆናል። ምሳሌ ምዕራፍ ዘጠኝ ቁጥር አሥራ ሰባት:- «ልጅህን ቅጣ ዕረፍትንም ይሰጥሃል፤ ለነፍስህም ተድላን ይሰጣታል» ይላል።

### የልጅን ጸባይ ለማረም በበትር መጠቀም

ጌታ በነዚህ ቃላት ውስጥ የተናገረውን በእውነት እንድታደርጉ የሚፈልግ መሆኑን ታማንላችሁን? በእውነት ልጆቻችሁን ብትወድዱና ልጆቻችሁን በሚመለከቱ ነገሮች ላይ ጌታ ያዘዘውን መጠበቅ ብትፈልጉ፥ አንዳንድ ጊዜ ልጆቻችንን በዱላ እንድንመታቸው ይፈልጋል ማለት ነው ብላችሁ ታስባላችሁን? ልጆቻችሁን ጸባያቸውን ማረምና መገሥጽ እንዳለባችሁ ታምናላችሁን? እርሱም የሚለው ይህንኑ ነው። በተጨማሪም በእምነት ቃሉን ብንታዘዝ እርሱም ልጆችን በማሠልጠን በኩል የገባውን የተስፋ ቃል እንደሚፈጽመው እናውቃለን።

ያንን የምናምን ከሆነ እግዚአብሔር ያወጣውን መመሪያ መከተል አለብን። ቀላል መስሎ ይታያችኋልን? ይህም ማለት ልጃችሁን አንድ ነገር እንዲያደርግ በምትጠይቁት ጊዜ ወይም «ወዲህ ና» ወይም «አትንካ» ወይም «አስቀምጥ» ብላችሁ ስታዝዙት ትእዛዞችን መፈጸሙን

መከታተል አለባችሁ። ሳትጮኹ መጠነኛ በሆነ ድምጽ በምታዙት ጊዜ ወዲያውኑ ካልታዘዛችሁ፥ በእርጩሜ ትእዛዙን እንዲፈጽም ማድረግ አለባችሁ።

ሰነፍ የሆነ ፍቅር ከዚህ የቀለለ መንገድ ይፈልጋል፥ እውነተኛ ፍቅር ግን መታዘዝን በቀላሉ ማስተማር እንደማይቻል መቀበል አለበት። ዕብራውያን 12:5-7:- «ጌታ የሚወደውን ይቀጣዋልና፥ የሚቀበለውንም ልጅ ሁሉ ይገርፈዋል . . . ለመቀጣት ታገሡ፤ እግዚአብሔር እንደ ልጆች ያደርግላችኋልና፤ አባቱ የማይቀጣው ልጅ ማነው?» ይላል። እግዚአብሔር ልጆችን እየቀጣ እንደሚያሠለጥን እኛም እንዲሁ ማድረግ አለብን።

## ከቅጣት በኋላ ማጽናናት

ልጃችሁን ከቀጣችሁ በኋላ ወዲያውኑ እቅፍ አድርጋችሁ የፍቅር ሁኔታ ማሳየት፥ ዕንባውን ማበስና መታዘዝም እንዳለበት መግለጽ አለባችሁ። ትንቢተ ሆሴዕ 6:1:- «ኑ ወደ እግዚአብሔር እንመለስ እርሱ ሰብሮናልና፥ እርሱም ይፈውሰናል፤ እርሱ መትቶናልና እርሱም ይጠግነናል» ይላል።

ይህ ጊዜ ከልጁ ጋር ሁለተኛ ወደዚህ ዓይነት አለመታዘዝ ውስጥ እንዳይወድቅ ጌታ እንዲረዳው ለመጸለይ አመቺ ጊዜ ነው። ልጃችሁንም እንዲጸልይ ልታበረታቱትም ትችላላችሁ። ከልጃችሁ ጋር የምታሳልፉት ይህ የጸጥታ የእርጋታ ጊዜ ከልጃችሁ ጋር የመንፈስ መቀራረብ ሊፈጥርላችሁና ያም መንፈስ በቀረው የሕይወት ዘመኑ ሁሉ በትክክለኛው መንገድ እንዲራመድ ይረዳዋል።

ይህ ነው በበትር የሚገኘው በረከት። አንድ ጊዜ ከተጠቀምንበት በኋላ ሁኔታውን በሙሉ ጭራሽ ረስተን በወላጅና በልጅ መሃከል ቀድሞ የነበረው ኅብረት ወዲያውኑ ይመለሳል። አለመታዘዝን ለማስተካከል እንዲህ ዓይነቱን ቅጣት ተጠቅማችሁ የማታውቁ ከሆነ እንደዚህ ያሉ አስደናቂ ውጤቶች እንደሚገኙበት ላታምኑ ትችላላችሁ። በወላጅና በልጅ መሃከል ያለው መለያየት ይወገዳል፤ አንድነታችሁም እንደገና ይመለሳል። በተጨማሪም በልጁ ውስጥ ያለው የጥፋተኝነት ስሜት ይፋቃል።

## ውጤት የሚያስገኝ የጸባይ እርማት በቁጣ ሊሰጥ አይቻልም።

አነስተኛ ለሆነው አለመታዘዝ እርጩሜ በምትጠቀሙበት ጊዜ፥ እናንተ ልጁን የምትቀጡት እርሱን የማረም ዓላማ ስላላችሁ እንጂ ተቆጥታችሁ ባለመሆኑ በልጃችሁ አእምሮ ውስጥ «ቅጣት የምቀጣው ጥፋት ስላጠፋሁ ሳይሆን ወላጆቼን የሚያስቆጣ ሥራ ስለሠራሁ ነው» የሚል አሳብ እንዲፈጠር አያስፈልግም። ወላጅ ቅጣትን የሚሰጠው ልጁን ለማረም የተወሰነ ዓላማ ስላለው በመሆኑ ቅጣቱ መሰጠት ያለበት በወላጅም ሆነ በልጅ ውስጥ የቁጣ መንፈስ ሳይኖር ነው።

እንዲህ ዓይነት ቅጣት በምትጠቀሙበት ጊዜ የልጁን መንፈስ ተስፋ ያስቆርጠዋል ብላችሁ ትፈሩ ይሆናል። እርግጥ ነው፥ ተመጣጣኝ ባልሆነና በንዴት በመማታት በጣም አደገኛ ሊሆን ይችላል። ይህ የእኔ ፈቃድ ያሸንፍ የአንተ ፈቃድ ይሸነፍ የሚል የፈቃድ ውጊያ ነው። የማንኛውም ፈቃድ እንደሚያሸንፍ ውጤቱን ይገልጻል። በእንደዚህ ያለ ጦርነት ወላጆች በዕድሜም በጉልበትም ከልጆቻቸው ስለሚበልጡ አብዛኛውን ጊዜ ድሉ የእነርሱ ነው። ነገር ግን በዚህ ጊዜ ልጁ ተስፋ የሌለውና የተደቆሰ መስሎ ይሰማዋል። ከዚያም በኋላ በዘመናት በልቡ መራራነትና ቂምን ይዞ ሊኖር ይችላል።

በፍቅር የሚሰጥ ትምህርት ግን ለልጁ ጥቅም ነው ተብሎ በእግዚአብሔር ቃል መሠረት የተደረገ ስለሆነ ልጁን ሥነ ሥርዓት ከማስያዙም በላይ የልጁን ጸባይ ያጎለምሰዋል። በሥነ ሥርዓት የታነጸ መንፈስ ነው እስከ መጨረሻው ድረስ በነፃነት ሊያብብ የሚችለው። ምክንያቱም መጨነቅና ቅሬታ በእርሱ የሉምና።

ማሠልጠን ትጋትን ይጠይቃል።

እንዲህ ዓይነቱን ሥራ ለማከናወን ብዙ ትጋት ይጠይቃል። ለዚህ ነው በራሳችሁ ብርታት ልትሠሩት የማትችሉት። ክርስቶስን ከመታዘዝ በቀር ሌላ ምንም ሃሳብ ሊኖራችሁ አይችልም። መልካም ጸባይ ያላቸው ልጆች እንዲኖሯችሁ ያላችሁ ፍላጎት ያ ብቻውን አያዘልቃችሁም። ያም ነገር ትክክል እስኪሆን ብቻ ነው። ለምሳሌ በሚደላችሁ ወንበር ላይ ተቀምጣችሁ ሳላችሁ ከልጆቻችሁ አንዱ ማድረግ የሌለበትን ነገር ሲሠራ ታያላችሁ። «እዚያ ጨርቅ ላይ አትንተት! ራዲዮኑን መሬት ትጠለዋልህ!» ትሉታላችሁ። እርሱ ግን መነተቱን ይቀጥላል። ከዚያ ከሚደላ መቀመጫ በመነሣት፥ እርጩሚ ፈልጋችሁ ልጁን መቅጣት ይኖርባችኋል። ከዚያ በኋላ የሠራው ስሕተት ምን እንደነበረ ግለጹለትና አጽናኑት። መጽሐፈ ምሳሌ ምዕራፍ አሥራ ሦስት ቁጥር ሃያ አራት:- «ልጁን የሚወድ ግን ተግቶ ይገስጸዋል» ይላል።

ሳታስቡት ልጆቻችሁ ደስተኞችና ለሌሎች ሰዎችም የሚያስቡ ሆነው ታገኙዋቸዋላችሁ። ዕብራውያን 12፡11:- «ቅጣት ሁሉ ለጊዜው የሚያሳዝን እንጂ ደስ የሚያሰኝ አይመስልም፥ ዳሩ ግን በኋላ ለለመዱት የሰላምን ፍሬ እርሱም ጽድቅን ያፈራላቸዋል» ይላል።

ቆላስይስ 3፡21:- «አባቶች ሆይ፥ ልባቸው እንዳይዝል ልጆቻችሁን አታበሳጩአቸው» ይላል። ልጆች በሚያድጉባቸው ዓመታት ውስጥ ከሚገጥሙአቸው የሚያበሳጩና ተስፋ የሚያስቆርጡ ነገሮች አንዱ ወላጆቻቸው ጽኑ አሳብ የሌላቸው ሆነው ማግኘታቸው ነው። ለምሳሌ አንድ ቀን ስለ አለመታዘዛቸው ብትቀጡአቸው በሌላ ቀን ደግሞ እንታዘዝም ካሉ አሳባችሁን ሳትለውጡ ቅጡአቸው። ለአንድ አለመታዘዝ ቀጥታችሁ ለሚቀጥለው ደግሞ አትለፉአቸው። አለዚያ ልጆቻችሁ ግራ ይገባቸውና በእነርሱ ላይ ያላችሁን ሥልጣን መቃወም ይጀምራሉ። በውስጣቸው የብስጭት ስሜት ይሰማቸውና ተስፋ መቁረጥ ይጀምራሉ።

ልጆቻችሁን የምታሰለጥኑባቸው ሌሎችም ዓይነት ሁኔታዎች አሉ። ሁልጊዜ ልጆቻችሁን በትሕትናና በአክብሮት ተቀብሉአቸው። የተስፋና የመበረታታት ስሜት እንዲኖርባቸው አድርጉ። ኃላፊነት እንዲሰማቸውም አስተምሩአቸው። በእነርሱ ፊት በታማኝነትና በግልጽ ኑሩ። ቤታችሁን በአስቂኝ ነገር ሙሉት። በፊታችሁ ክብር ያላቸው መሆናቸውን እንዲሰማቸው አድርጉ። እነዚህ ሁሉ የተመሠረቱት በመታዘዝ መሠረት ላይ ነው።

ለልጆቻችሁ መታዘዝን ዘወትር ለማስተማር መትጋት አለባችሁ። ለልጃችሁ አንድ ትእዛዝ ከሰጣችኋቸው እንዲፈፅሙት ማድረግ አለባችሁ። ሁላችሁም ተመቻችታ በእሳት አጠገብ የተኛችን ድመት ሳታዩ አልቀራችሁም። የተኛች ትመስላለች። ነገር ግን በቤት ውስጥ በየትኛውም በኩል አይጥ ስትሄድ ብታይ ወዲያውኑ ትነቃና ዘላ ልትይዛት ትዘጋጃለች።

ወላጆችም ለልጆቻቸው የተዝናና አስደሳች የሆነ የኑሮ ሁኔታ መፍጠር አለባቸው። ነገር ግን ማንም አልታዘዝም ቢል፥ ወይም የወላጆችን ሥልጣን ቢቃወም ወዲያውኑ አስፈላጊው ነገር መደረግ አለበት። ልጆቻችንን እንዴት አድርገን እንደምናሳድግ እግዚአብሔር የፈቀደ

መሆኑን የሚያሳየንን መጽሐፍ ቅዱስን በእምነት ብንታዘዝ መልካም ውጤቶችን እንድናገኝ በእርሱ ላይ ልንታመንበት እንችላለን።



## ክፍል 3 - ትምህርት 10
## እግዚአብሔርንና ሰውን ማክበር

ዓላማ፡- ልጆች እግዚአብሔርንና ሰውን እንዲያከብሩ መመሪያና ምክር ለመስጠት።

በቃል የሚጠና ጥቅስ፡- «ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ ቅዱስ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ምድር ሁሉ ከክብሩ ተሞልታለች» ኢሳ. 6፡3

መግቢያ፡- ኢሳይያስ ታላቁ ንጉሥ ከሞተ በኋላ በፍርሃትና በጭንቅ ውስጥ ሆኖ እግዚአብሔርን በጸሎት ይፈልግ ነበር። ድንገት ሰማይን በራእይ ይመለከት ጀመር። ጌታ እግዚአብሔር ከፍ ባለው ዙፋኑ ላይ ተቀምጦ፥ መቅደሱም በክብሩ ተሞልቶ ተመለከተ። ስድስት ክንፎች ያሉአቸው ኃያላን ሱራፌልም ከእርሱ ጋር ነበሩ። በሁለቱ ክንፎቻቸው ፊቶቻቸውን፥ በሌሎቹ በሁለት ክንፎቻቸው እግሮቻቸውን ሸፍነው በቀሩት በሁለቱ ክንፎቻቸው ደግሞ ይበሩ ነበር። ግርማ በተሞላው ሁኔታም እየተቀባበሉ «ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ ቅዱስ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር፥ ምድር ሁሉ ከክብሩ ተሞልታለች» እያሉ ይዘምሩ ነበር። ምን ዓይነት የሚያስገርም መዝሙር ነበር! ቤተ መቅደሱን እስከ መሠረቱ ድረስ አናወጠው፤ በድንገትም የቤተ መቅደሱ ውስጠኛው ክፍል በጢስ ተሞላ።

ኢሳይያስ የሱራፌልን ዝማሬ ሲሰማ እግዚአብሔር እርሱ ሊመለከተው የማይችለው ቅድስ ክብር እንዳለው አይቶ በፍርሃት ተሞላ። የእግዚአብሔርን ክብር በሚመለከትበትና ስለ ቅድስናው በሚሰማበት ጊዜ «ከንፈሮቼ የረከሱብኝ ሰው በመሆኔ ከንፈሮቻቸው በረከሱባቸው ሕዝብ መካከል በመቀመጤ ዓይኖቼ የሠራዊትን ጌታ ንጉሡን እግዚአብሔርን ስለ አዩ ጠፍቻለሁና ወዮልኝ!» ብሎ ጮኸ።

ኢሳይያስ በጣም ፈራ፤ ስለ ራሱም ሁኔታ በጣም አዘነ። ከሱራፌልም አንዱ እየበረረ ወደ መሠዊያው ሄደና በጉጠት የሚነድ ፍም አነሣ። በፍሙ የኢሳይያስን ከናፍርት ዳበሰና «በደልህ ከአንተ ተወገደ፥ ኃጢአትህም ተሠረየልህ» ብሉ ተናገረው።

ኢሳይያስ የእግዚአብሔርን ክብር አየ፤ ስለ ቅድስናውም ሰማ። ከዚህም የተነሣ ንስሐ ገባ ከኃጢአቱም ነጻ።

### እግዚአብሔርን መፍራት ከኃጢአት ይጠብቃል።

ኃጢአት ለተሞላበትና በግድየለሽነት ለተያዘ ሕይወት እግዚአብሔር ቅዱስና ጻድቅ ሁሉንም የሚያይ እንደሆነ ከማወቅ የበለጠ ኃጢአት እንዳይሠራ የሚያግደው ምንም ነገር የለም።

አቶ ሰሎሞን ለቤተሰቡ ከመዝሙረ ዳዊት 138/139/፡1-5 «አቤቱ መረመርኸኝ ዐወቅኸኝም። አንተ መቀመጤንና መነሣቴን ዐወቅህ፤ አሳቤን ሁሉ ከሩቅ አስተዋልህ። ፍለጋዬንና ዕረፍቴን አንተ መረመርህ፤ መንገዶቼን ሁሉ ቀድመህ አወቅህ» የሚለውን ከቁጥር 1-3 ያለውን ክፍል አነበበ። ቆም ብሎ ዙሪያውን ተመለከተና «እግዚአብሔር በእያንዳንዷ ቅጽበት የት እንዳለን ያውቃል፤ ምን ለመናገር እንደፈለግን ከመናገራችን በፊት አስቀድሞ

ያውቀዋል፤ እግዚአብሔር ስለ እኛ ሁሉን ነገር ማወቁ የሚያስገርም ነገር አይደለምን? አሳባችንን ሁሉ ያውቃል፤ የምንናገረውን ሁሉ ይሰማል» አለ።

ሙሉነሽ ደስ አላላትም። ከአንድ ጊዜ በላይ ሳይታወቅባት አልታዘዝም ያለችበት ጊዜ ነበረ። እናቷ ሕፃኑን ተስፋዬን እንድትጠብቅ ለእርስዋ ትታላት ስትሄድ አንዳንድ ጊዜ ሹልክ ብላ ትወጣና ከጎረቤት ልጆች ጋር ትጫወት ነበር። መጥፎ ነገሮችን ታስባለች፤ አንዳንዴ ደግሞ መጥፎ ነገሮችን ትናገር ነበረ። ያንን ሁሉ እግዚአብሔር አይቶታል፤ ሰምቶታል ማለት ነውን? ወደ አባቷ ተመለከተችና «ብዙ መጥፎ ነገሮችን አድርጌአለሁኝ። እግዚአብሔር በእኔ ሳያዝን አልቀረም። ይቅርታ እንዲያደርግልኝ ልጠይቅና ጌታ ኢየሱስን እንደ ግል አዳኜ አድርጌ ልቀበለው እችላለሁን?» ብላ ተናገረች።

አቶ ሰሎሞን ልጆቹ ራሳቸው ደኅንነት ለመቀበል ፈልገው እንዲጠይቁ አስቀድሞ ጸልዮአል። በጣም ደስ እያለው ከሙሉነሽ ጋር አብረው ጸለዩ። በመጀመሪያ «ውድ ፈጣሪዬ ሆይ ብዙ ጊዜ ኃጢአት ሠርቼአለሁ፤ አንተንም አሳዝኜሃለሁ። ልታየኝ እንደምትችል አላወቅሁም ነበረ። እባክህ ይቅርታ አድርግልኝ። ኢየሱስ ወደ ሕይወቴ እንዲመጣና በውስጤ እንዲኖር ልጅህም እንዲያደርገኝ እፈልጋለሁ። አሜን» ብላ ጸለየች። ከዚያም አቶ ሰሎሞን እግዚአብሔር ለልጁ ልብ ስለ ተናገረ ልጁም እንድትሆን ወደ እርሱ ቤተሰብ ስለ አመጣት እግዚአብሔርን በጣም በማመስገን ጸሎት አደረገ።

እንደገናም መጽሐፍ ቅዱስን ከፈተና «ነፍሴ ሆይ እግዚአብሔርን ባርኪ አጥንቶቼም ሁሉ የተቀደሰ ስሙን፥ ነፍሴ ሆይ እግዚአብሔርን ባርኪ፥ ምስጋናውንም ሁሉ አትርሺ፤ ኃጢአትሽን ሁሉ ይቅር የሚል፥ ደዌሽንም ሁሉ የሚፈውስ፥ ሕይወትሽን ከጥፋት የሚያድናት፥ በምሕረቱና በቸርነቱ የሚከልልሽ፥ ምኞትሽን ከበረከቱ የሚያጠግባት ጎልማሳነትሽን እንደ ንስር ያድሳል» የሚለውን በመዝ. 102/103/ ከቁ. 1-5 የሚገኘውን ክፍልና በዚሁ መዝሙር በቁጥር 12ና 13 ላይ «ምሥራቅ ከምዕራብ እንደሚርቅ እንዲሁ ኃጢአታችንን ከእኛ አራቀ አባት ለልጆቹ እንደሚራራ እንዲሁ እግዚአብሔር ለሚፈሩት ይራራል» የሚለውን ክፍል አነበበ።

ልጆቹ ወደ መኝታቸው በሚሄዱበት ጊዜ ጸጥታ ሰፈነ። ሙሉነሽ አልጋዋ ውስጥ ገብታ ከመተኛትዋ በፊት ቀስ ብላ ወደ አባትዋ ጋ ሄደችና «ዛሬ በጣም ደስ ብሎኛል አባባ» አለችው።

## ልጆች እግዚአብሔርን ቤቱንና የቤተ ክርስቲያንን መሪዎች ማክበር መማር ይኖርባቸዋል።

ፈሪሃ እግዚአብሔር እየተሰማችሁ መጽሐፍ ቅዱሳችሁን ዘወትር ሳታቋርጡ ለልጆቻችሁ በምታነቡበት ጊዜ ልጆቻችሁ የእግዚአብሔርን ቃልና እግዚአብሔርን መፍራት ይማራሉ። ቤተ ክርስቲያንም የእግዚአብሔርን ቃል ማስተማሪያ፥ የእግዚአብሔር ቤት መሆኑን ስለሚያውቁ ቤተ ክርስቲያን በሚሄዱበት ጊዜ በጸጥታ ይቀመጣሉ። የቤተ ክርስቲያን መጋቢና ሽማግሌዎች የእግዚአብሔር አገልጋይ መሆናቸውን ስለሚያውቁ እነርሱንም ደግሞ ያከብሩአቸዋል።

ሁለተኛ ነገሥት ምዕራፍ 2 ቁ. 23-25 ስለ አንድ አሳዛኝ ታሪክ ይናገራል። ይኸውም ይኖሩበት ከነበረው ከተማ ወጥተው ወደ ቤቴል በሚወስደው ጎዳና ላይ ይጫወቱ ስለነበሩ ወጣቶች ነው። የእግዚአብሔር ነቢይ የሆነው ኤልሳዕ በዚያ መንገድ በሚያልፍበት ጊዜ «አንተ መላጣ ውጣ! አንተ መላጣ ውጣ!» እያሉ መጮህ ጀመሩ። ወደ እነርሱም ዘወር አለና

በእግዚአብሔር ስም ረገማቸው። ከጫካ ውስጥም ሁለት ድቦች ወጡና ከወጣቶቹ ውስጥ አርባ ሁለቱን በኃይል ሰባበሩአቸው።

እግዚአብሔር ያንን ታሪክ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለምን እንደ አጻፈው ታውቃላችሁን? ልጆቻችን አክብሮት የጎደላቸውና ባለጌ ሆነው እንዳያድጉ ሊያስጠነቅቀን አይደለምን?

## ልጆች ወላጆቻቸውን ማክበር አለባቸው።

እግዚአብሔር «እናትና አባትህን ማክበር አለብህ» ይላል፤ ዘሌ. 19፡3። ይህ የተጻፈው ለሁሉም ሰው ነው። በዘጸአት 20፡12 ውስጥ እግዚአብሔር «አባትና እናትህን አክብር» ይላል። ከዚያም ቀጥሎ «እግዚአብሔር አምላክህ በሚሰጥህ ምድር ላይ ዕድሜህ ይረዝማል» የሚል የተስፋ ቃል ይሰጣል። ይህ ትእዛዝ በኤፌ. 6፡2-3 ውስጥ ተደግሟል። በመጀመሪያ እናንተ እናትና አባታችሁን የምታከብሩ መሆናችሁን እርግጠኛ ሁኑ፥ ከዚያ ቀጥሎ ልጆቻችሁ ይህንን ትእዛዝ እንዲያከብሩ የእናንተ እርዳታ ያስፈልጋቸዋል። አባት ትእዛዝ ሲሰጥ ልጅ ወዲያውኑ ባይታዘዝ እናት ደግሞ ልጁ እንዲታዘዝና አባቱን ማክበር ያለበት መሆኑን እንዲያስታውስ መርዳት አለባት። ልጅ አንድ ነገር እንዲያደርግ እናት በምታዝበት ጊዜም አባት ተመሳሳይ ነገር ማድረግ አለበት። አባትየው የእናትየዋን ቃል መደገፍና እናቱን መታዘዝና ማክበር ያለበት መሆኑን መምከርና መርዳት አለበት።

## ልጆች ሌሎችን እንዲያከብሩ መማር አለባቸው።

በዘመናችን ሰዎችን ያለማክበር ዝንባሌ ይታያል። እግዚአብሔር ግን «በሽበታሙ ፊት ተነሣ፤ ሽማግሌውንም አክብር፥ አምላክህንም ፍራ፤ እኔ እግዚአብሔር ነኝ» ይላል፤ ዘሌ. 19፡32። መጽሐፍ ቅዱስ «በሕዝብህ አለቆች ላይ ክፉ ቃል አትናገር» ይላል፤ የሐዋ. ሥራ 23፡5። እንደገናም ደግሞ «ነፍስ ሁሉ በበላይ ላሉት ባለ ሥልጣኖች ይገዛ ከእግዚአብሔር ካልተገኘ በቀር ሥልጣን የለም፤ ያሉትም ባለ ሥልጣኖች በእግዚአብሔር የተሾሙ ናቸው» ይላል፤ ሮሜ 13፡1-5ን አንብብ። በሥልጣን ላይ የተቀመጡት ሁሉ በእግዚአብሔር ፈቃድ የተቀመጡ ስለሆኑ ልናከብራቸውና ልንጸልይላቸው ይገባል።


## የሌሎችን ንብረት ማክበር

እራሳችን ምሳሌ በመሆን ልጆቻችን የሰዎችን መብትና ንብረት እንዲያከብሩ ልናስተምራቸው እንችላለን። ልጅ በጣም አጥፊና ግድ የለሽ ሊሆን ይችላል። የሌላ ሰውን ንብረት ልጆች እንዲያከብሩ ለማስተማር መወሰድ ያለባቸው ሁለት እርምጃዎች አሉ።

1. የልጆቻችሁ የሆኑትን ንብረቶች አክብሩ። እነርሱ የሚለብሷቸውን ልብሶች እነርሱ ብቻ እንዲለብሱ አድርጉ። አንድ ነገር የእነርሱ እንዲሆን ከሰጣችሁ የእነርሱ ንብረት እንደሆነ አድርጋችሁ ቁጠሩላቸው። ለምሳሌ ኳስ ቢሆን ለሌሎች ማጫወት መማር እንዳለበት፤ ነገር ግን ኳሱ ሁል ጊዜ ለእርሱ መመለስ አለበት፥ ኳሱንም የሚያስቀምጥበት ሥፍራ እንዲኖረው ያስፈልጋል።

2. በቤተሰብ ውስጥ የሌሎች የሆነውን ንብረት እንዲያከብር አስተምሩት፥ ለራሱ ንብረት ጥንቁቅ መሆን እንዳለበት ሁሉ እንደዚሁም በቤተሰብ ውስጥ ላሉት ሰዎች ንብረት ጠንቃቃ መሆን አለበት።

እግዚአብሔር «ሁሉን አክብሩ ወንድሞችን ውደዱ፥ እግዚአብሔርን ፍሩ» ይላል፤ 1ኛ ጴጥ. 2፡17።



# ክፍል 3 - ትምህርት 11

## እውነተኛነትና ታማኝነት

ዓላማ:- ወላጆች በልጆቻቸው ሕይወት ውስጥ የእውነተኝነትና የታማኝነት መሠረት እንዲጥሉ ለማበረታታት።

በቃል የሚጠና ጥቅስ:- «ውሸተኛ ከንፈር በእግዚአብሔር ዘንድ አስጸያፊ ነው፤ እውነትን የሚያደርጉ ግን በእርሱ ዘንድ የተወደዱ ናቸው።» ምሳሌ 12፡22

መግቢያ:- ወይዘሮ ሣራና እኅቷ በፀሐይ እንዲደርቅ ተሰጥቶ የነበረውን በርበሬ ለማስገባት ይጣደፉ ነበር። ዝናብ መጥቶ ስለነበር ወ/ሮ ሣራ በርበሬ የተሰጣበትን ሰሌን በአንድ በኩል እኅቷ ደግሞ በሌላ በኩል ይዘው የኋሊት ወደ ቤት ሲያስገቡ በድንገት ትንሿን ጠረጴዛ ገፉ ሲያደርጓት ወደቀች፤ በላይዋ ላይ መጻሕፍት፥ ወረቀቶችና ራዲዮኑ መሬት ወደቁ። ራዲዮኑ በሚወድቅበት ጊዜ በአንድ ጎኑ ሲሚንቶው ወለል ላይ በኃይል ተከሰከሰና ተንከባሎ በፊቱ በኩል ወለሉ ላይ ወደቀ።

ሣራና እኅትዋ ተደናግጠው ቆሙ። ወዲያውኑ የያዙትን ሰሌን አስቀመጡና ወ/ሮ ሣራ ራዲዮኑን ብድግ አድርጋ ከፈተችው። ምንም ድምጽ የለውም፤ ብታንቃንቀውም ውስጡ ከመንኳኳቱ በቀር ምንም ድምጽ አልሰጠም። በጣም ፈራች። ባለቤቷ አቶ ዓለሙ ሲመጣ ምን ይል ይሆን? ራዲዮኑን የገዛው ለብዙ ጊዜ ገንዘብ ከአጠራቀመ በኋላ ነው።

አቶ ዓለሙ ቀኑን ሙሉ ሥራውን ሲሠራ ውሎ ወደ ቤቱ መጣ። በጣም ደክሞትና እርቦት ስለነበር የፈለገው ትንሽ ተቀምጦ ራዲዮ ካደመጠ በኋላ እራቱን በልቶ ለመተኛት ነበር። ወንበር ላይ ከተቀመጠ በኋላ ራዲዮኑን ከፈተ። ምንም ድምጽ አልነበረም። ቢያንቃንቀውም ምንም ድምጽ አልሰጠም «ምን ነካው?» ብሎ ጠየቀ። ማንም መልስ አልሰጠውም።

«ራዲዮናችንን ምን አረጋችሁት?» ብሎ ጠየቀ። እንደገና ምንም መልስ አላገኘም።

«ደህና! ምንም ነገር አትናገሩም ማለት ነው? ራዲዮኑን የሰበረው ማን ነው?» ብሎ እንደገና ጠየቀ። አሁንም መልስ የለም። አቶ ዓለሙ ንዴት ተሰማው። ምን እንደነካው ለምን አይነግሩኝም? ብሎ አሰበ።

የተለያየ ዓይነት ውሸት አለ አይደለምን?

### እግዚአብሔር የሚዋሹ ከናፍርትን ይጠላል።

ዳዊት በመዝ. 118/119/ ቁጥር 104ና 108 «የሐሰትን መንገድ ጠላሁ» ብሎ ይናገራል። በዛሬው ጥቅሳችን የሚዋሹ ከናፍርትን እግዚአብሔር የሚጠላ መሆኑን እንመለከታለን። ሐሰትን እንደ ትንሽ ነገር አድርገን እንቆጥር ይሆናል፤ እግዚአብሔር ግን አይቆጥረውም። በቀጥታ ሐሰት ልንናገር ወይም ወ/ሮ ሣራና እኅትዋ እንዳደረጉት በሐሰት ውስጥ መኖር እንችላለን። ነገር ግን ይህም ቢሆን መዋሸት ነው። ውሸት የተለያዩ ዓይነት መልክ አለው . . . መዋሸት፥ ማታለል፥ የሐሰት ምልክት መስጠት፤ በሐሰት መመስከር። ውሸታምነት ጸባይ ሆኖ ከመለመዱ በፊት ወላጆች ነቅተውበት ማስተካከል አለባቸው። ሁልጊዜ ውሸት

የመናገር ልምድ ያለባቸው ሰዎች ውሸት መናገር ለምዶባቸው ነው እንጂ ሌላ ምንም ምክንያት የላቸውም። ማንም እነርሱ የሚነገሩትን ቃል አያምንም።

እንደገናም በቃል የሚጠናው ጥቅሳችንም «እውነትን የሚያደርጉ ግን በርሱ ዘንድ የተወደዱ ናቸው» ይላል። «እነሆ እውነትን ወደድህ» የሚለው በመዝ. 50/51/:6 የሚገኘው ጥቅስ ደግሞ እግዚአብሔር እውነትን የሚወድ መሆኑን ያስታውሰናል። በማናቸውም ዓይነት መንገድ ሐሰትን እንድንናገር የሚመጣብንን ፈተና ሁሉ መቋቋም አለብን። መዋሸት ከልጅነታችሁ የጀመራችሁ ልማድ ከሆነ ተናዘዙትና ከሕይወታችሁ እንድታስወግዱት ኃይል እንዲሰጣችሁ እግዚአብሔርን ጠይቁት። ከዚያ በኋላ ልጆቻችሁን በእውነተኛው መንገድ ልትመሯቸው ትችላላችሁ።

## ለልጆቻችን የገባነውን ቃል መጠበቅ አለብን።

ልጆቻችን እኛን ስለሚመለከቱና የምንናገረውን ሁሉ ስለሚያጤኑት፥ ንግግራችንን ማረም ይኖርብናል የተናገርነውንም መፈጸም አለብን። ምናልባት ወንዱን ልጃችሁን «ቅዳሜ ሥራ ስለማልሄድ አያትህ ጋ እወስድሃለሁ» ትሉት ይሆናል። ቅዳሜ ይመጣል። ነገር ግን የገባችሁለትን ቃል ረስታችሁ ከጓደኞቻችሁ ጋር ወደ አንድ ቦታ እንድትሄዱ ስለ ጋበዙዋችሁ ስለ ልጃችሁ ምንም ነገር ሳታስቡ ትሄዳላችሁ። በዚህን ጊዜ ልጃችሁ ምን ይሰማዋል? ሌላ ጊዜ የምትናገሩትን ቃል ያምናልን?

## ስለ ውሸት እግዚአብሔር የሚናገረውን ማስተማር አለብን።

እግዚአብሔር ክርስቲያኖችን «እርስ በእርሳችሁ ውሸትን አትነጋገሩ» ሲል ተናግሮአቸዋል፤ ቆላ. 3:9። የእግዚአብሔር ልጆች እንደመሆናችን መጠን እግዚአብሔር ኃጢአትን እንደሚጠላ፥ እኛም ኃጢአትን መጥላት አለብን። እግዚአብሔር በራዕይ 21:27 ላይ ውሸታሞች፥ ወደ መንግሥተ ሰማያት እንደማይገቡ ተናግሯል። እንደገና በራዕይ 22:14-15 ባለው ክፍል ውስጥ ውሸተኞች በውጪ እንደሚሆኑና ወደ መንግሥተ ሰማያት እንደማይገቡ በገለጸበት ጊዜ ይህንኑ ሃሣብ በድጋሚ ተናግሮታል። በመጽሐፈ ምሳሌም 6:16-19 ላይ እንደተጻፈው እግዚአብሔር ስለሚጠላቸው ሰባት ነገሮች ይነግረናል፤ ከእነዚህም አንዱ ሐሰተኛ ምላስ ነው። በተጨማሪም በ ኤፌ. 4:25 ላይ እንደተገለፀው አሁን የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንንና አንዱ የሌላው አካል ስለሆንን ውሸትን አስወግደን እውነትን እንድንነጋገር ያስተምረናል።

## እግዚአብሔር ስለ ስርቆት ምን ይላል?

በኦሪት ዘጸአት 20:15 ላይ «አትስረቅ» ይላል። ለማስተማር ቀላል ከሆኑት ነገሮች አንዱ፥ ለልጆች አለመስረቅን ማስተማር ነው፤ መታዘዝን ከማስተማር ይልቅ ቀላል ነው። ብዙዎች ወላጆች ይህን አለማወቃቸው የሚያሳዝን ነው። መስረቅ የሌለባቸው መሆኑን አንዳንድ ወላጆች ለልጆቻቸው ማስተማር ጠቃሚ መስሎ የማይሰማቸው መሆኑ ይበልጥ የሚያስገርም ነው። እንዲያውም ታማኝ አለመሆንን ወይም ማጭበርበርን የሚያስተምሩ ወላጆች እንኳን ሳይኖሩ አይቀርም።

አንድ ነገር በምትሰረቁበት ጊዜ የሚሰማችሁ ስሜት ምንድነው? ስለ ሌባው ምን ታስባላችሁ? በእርግጥ ልጃችሁ ሌባ እንዲሆን አትፈልጉም። በአንድ በተወሰነ ጊዜ ልጆች ሁሉ የራሳቸው ያልሆነውን ዕቃ ይወስዳሉ። በመጀመሪያ ስለ ባለቤትነት ምንም ነገር ስለማያውቁ

እንዳንዱ ዕቃዎች የሌሎች ሰዎች መሆናቸውን ማስተማር ይኖርባችኋል። የሌላ ሰው የሆኑትን ዕቃዎች በጭራሽ መንካት እንደሌለባቸው መማር ይኖርባቸዋል።

ልጃችሁ የራሱ ያለሆነውን አንድ ነገር ይዞ ወደ ቤት ቢመጣ ወዲያውኑ እንዲመልስ ማድረግ አለባችሁ። እናንተ እራሳችሁ አትመልሱ። እርሱ እራሱ ሄዶ እንዲመልስ አድርጉ። የሚያደርገውን ነገር ማየት ቢያስፈልግ አብራችሁት ሂዱ። የሌላ ሰው ንብረት ወዲያውኑ መመለስ እንዳለበት አስረዱት። በመጨረሻ ስሕተት መሆኑን ከተረዳ እንደገና ሰርቆ ሲገኝ ወዲያውኑ መቀጣት አለበት።

ወዲያውኑ ይህን ጸባይ ትቶ ታገኙታላችሁ፤ ነገር ግን ከጊዜ በኋላ እንደዚህ ዓይነቱን ስሕተት እንደገና መሥራት ይጀምራል። በወቅቱ ወዲያውኑ ጸባዩን ማረም አለባችሁ። መስረቅ ትንሽ ነገር እንደሆነና ዋጋ የማይሰጠው መሆኑን እንዲያስብ በጭራሽ አትፍቀዱለት። ትናንሽ የሆኑ ስርቆቶችን እንዲያርም ካላደረጋችሁ እያደገበት ይሄዳል።

በት/ቤት ውስጥ መኮረጅ ማለት ማጭበርበር፥ መስረቅና መዋሸት መሆኑን ለልጆቻችሁ አስተምሩዋቸው። መኮረጅ 1/ ሌላ ሰው የሠራበትን በመውሰድ መስረቅ ሲሆን 2/ እራሳቸው እንደሠሩ አድርገው በማስመሰል ማቅረባቸው እንደመዋሸት ያህል ይቆጠራል።

ከሁሉ በፊት ወላጆች እንደመሆናችን መጠን ታማኝና እውነተኛ ሆነን መገኘት አለብን። ያን ጊዜ እነዚህ ነገሮች በልጆቻችን ሕይወት ውስጥ እንዳይገኙ ጥንቁቅ ሆነን ነቅተን ልንጠብቅ እንችላለን። መታዘዝን ወይም ሌሎቹን ጸባያት ለማስተማር ትጉሕ በሆንበት መጠን ታማኝነትን፥ እውነተኛነትንና አለመስረቅን በጥንቃቄ ለማስተማርና በተማሩበት መንገድ ለመምራት ትጋት ሊኖረን ያስፈልጋል።

# ክፍል 3 - ትምህርት 12

## ቸርነትና ርኅሩኅነት

ዓላማ:- ወላጆችን በልጆቻቸው ፊት ቸርና ርኅሩኆች በመሆን አርአያ እንዲሆኗቸው ለመምራት። እነዚህ ጸጋዎች፥ ልጆች ሌሎች ሰዎች ለእነርሱ ቸርና ርኅሩሆች በሚሆኑላቸው ጊዜ ወዲያውኑ የሚማሩአቸው ናቸው።

በቃል የሚጠና ጥቅስ:- «እርስ በእርሳችሁም ቸሮችና ርኅሩኆች ሁኑ፥ እግዚአብሔር ደግሞ በክርስቶስ ይቅር እንዳላችሁ ይቅር ተባባሉ።» ኤፌ. 4:32።

መግቢያ:- የአራት ዓመት ዕድሜ ያላቸው መንትዮች ሚክያስና ሚሚ ከቤታቸው ጓሮ ባለው መስክ ኳስ ይጫወቱ ነበር። ሚክያስ ይዟት የነበረችውን ኳስ በጣም ይወዳት ነበረ፤ ኳሷ ቀይና በጣም ደስ የምትል ስትሆን ሚሚም ትወዳት ነበረ፤ ሚክያስ ኳሷን ከሚሚ ነጠቀና ያዛት ሚሚም ኳሷን መያዝ ትፈልግ ነበረ፤ ሚክያስ ኳሷን ከሚሚ ነጠቀና ያዛት ሚሚም ኳሷን መያዝ ትፈልግ ነበር። ሚሚ ሚክያስን ልትነጥቀው ሞከረች፤ እርሱ እየተሳደበ አመለጣት። እርሷም በኃይል እያለቀሰችና ጀርባውን እየደለቀች ተከተለችው።

### ራስ ወዳድነትንና ቁጣን አስወግዱ።

በአንዳንድ ቤት የሚክያስና የሚሚ ዓይነት ጸባይ ዘወትር ይታያል። በቤታችሁ ውስጥ እንዲህ ያለ ቢደረግ ምን ታደርጋላችሁ?

የዚህ ዓይነቱ ጸባይ ከዕድሜ ጋር የሚቀር ቀላል ነገር አድገራችሁ አትቁጠሩት። ዝም ብላችሁ አትለፉት። ለልጃችሁ አስተዳደግ በእግዚአብሔር ዘንድ ተጠያቂዎች ናችሁ፤ ስለዚህ በነገሩ ጣልቃችሁ መግባት አለባችሁ።

ልጆቻችሁ እንደዚህ ቢጣሉ ወዲያውኑ ጠርታችሁ እንዲህ ዓይነቱን ድርጊት ማቆም እንዳለባቸው ንገሩአቸው። እነርሱ እራሳቸው ሌሎች እንዲያካፍሏቸውና እንዲያደርጉላቸው የሚፈልጉትን ያህል ለሌሎችም ማካፈልና ማድረግ እንዳለባቸው ለልጆቻችሁ አስረዱአቸው። ኳሷን ውሰዱና ኳሱን ለቀማው እንደሚሰጠው አድርጋችሁ ቅጡት። ያለቀሰችውና የተማታችውም ልጅ ጥፋቷ ምን እንደሆነ እንድታስብ ለአሥር ደቂቃ ያህል ጸጥ ብላ እንድትቀመጥ ብታደርጉ ደህና ነው። ይህ መጥፎ ድርጊት በመተሳሰብና ርኅሩኆች በመሆናቸው ሊወገድ የሚችል መሆኑን አስረዱአቸው።

### መዝራትና ማጨድ

እግዚአብሔር በቃሉ በጣም አስፈላጊ የሆነ መመሪያ ሰጥቶናል። መመሪያውም በገላ. 6:7 ውስጥ ይገኛል። «ሰው የሚዘራውን ሁሉ ያንኑ ደግሞ ያጭዳል» ይላል። ጥላቻን ብትዘሩ የምታጭዱት እሱኑ ወይም ተመሳሳዩን ነው። ቸርነትንና ርኅራኄ ብትዘሩ ሌሎች ለእናንተ ቸርነትን ሲያደርጉላችሁ ታገኙዋቸዋላችሁ።

በቤታችሁ ውስጥ የቸርነትን ዘር ትዘራላችሁን? የዛሬው ጥቅሳችን «እርስ በእርሳችሁ ቸሮችና ርኅሩሆች ሁኑ» ይላል፥ ኤፌ. 4:32። ወላጆች እንደመሆናችሁ የምታደርጉት

ቸርነትና ርኅራኄ በልጆቻችሁ ሕይወት ውስጥ ተመሳሳይ ፍሬ ሲያፈራ ታያላችሁ። ስለ ስሜታቸው ይገዳችኋልን፤ በትንሽም ቢሆን ቸርነትን ታደርጉላቸውላችሁን? ይህንን በምታደርጉበት ጊዜ እነርሱም ለእናንተና ለሌሎች ሰዎች እንደዚህ ሲያደርጉ ታያላችሁ። እውነተኛ ቸርነት ለራሴ ማለትን አያውቅም፤ ራሱን ረስቶ ለሌሎች ያስባል።

## በየቀኑ በሕይወታችሁ ውስጥ የቸርነት ሥራ አሳዩ።

በጎረቤታችሁ ያሉት ሴትዮ በሚታመሙበት ጊዜ ምን ታደርጋላችሁ? ለጎረቤታችሁ ምግብ በምታዘጋጁበት ጊዜ ሴቷ ልጃችሁ እንድትረዳችሁ አድርጉ፤ ምግቡን አብራችሁ ለሴትየዋ አቅርቡ። ለተቸገረውስ ድኃ ምን ታደርጉለታላችሁ? በችግር ውስጥ ላለውና ዕርዳታ ለሚፈልገው ዘመዳችሁስ ምን ታደርጉለታላችሁ? በዚህ ዓይነት የቸርነት ሥራ ቤተሰባችሁ ማካፈል አለበት። ልጆቻችሁ ከመማሪያ መጻሕፍት ሊማሩ የማይችሉትን ጸባይ ታስተምሩዋቸዋላችሁ።

ኢየሱስ ለሕዝብ ይራራ ነበር። በሽተኞችን ፈወሰ፤ የዕውሮችን ዓይን አበራ፤ ስለ ሌሎች ይገደው ነበር፤ በሚያሳየውም ቸርነት ለእነርሱ ያለውን ፍቅር ይገልጽ ነበር። አንድ ጊዜ «ኢየሩሳሌም፥ ኢየሩሳሌም ሆይ! . . . ዶሮ ጫጩቶችዋን ከክንፎችዋ በታች እንደ ምትሰበስብ ልጆችሽን እሰበስብ ዘንድ ስንት ጊዜ ወደድሁ! አልወደዳችሁምም» ሲል ተናገረ፤ ማቴ. 23፡37። እኛም እንደ እርሱ ቸሮችና ርኅሩሆች ልንሆን ይገባናል።

## ትንሺ ምርኮኛ ሴት

የታላቁ የሶርያ የጦር ኃይል ምርኮኛ ሆና ተወስዳ የነበረችውን የእሥራኤላዊቷን ትንሽ ልጅ ታሪክ ታስታውሳላችሁን? በባርነት ነበር የምትኖረው፤ ነገር ግን ስለ ጌታዋ ስለ ንዕማን ታስብ ነበር። በንጉሡ ሠራዊት ውስጥ ኃይለኛ ቢሆንም እንኳ ለምጽ ነበረበት። በ2ኛ ነገ. 5፡3 ውስጥ «ጌታዬ በሰማርያ ካለው ከነቢዩ ፊት ቢደርስ ኖሮ ከለምጹ በፈወሰው ነበር» ብላ እንደተናገረች ተጽፏል። ንዕማንና በቤቱ ውስጥ ያሉት ሁሉ ምክሯን መቀበላቸው እጅግ በጣም ታማኝና ቸር በርኅራኄ የተሞላች ሰው እንደ ነበረች ያሳያል። ንዕማን ወደ እሥራኤል ሄዶ፤ በነቢዩ ኤልሳዕም ተፈወሰ። የቀረውን የታሪኩን ክፍል ከ2 ነገ. 5፡1-14 እራሳችሁ ልታነቡት ትችላላችሁ።

## ልጆቻችሁ ከመጥፎ ጓደኞች ጋር እንዳይገጥሙ ጠብቋቸው።

መጽሐፍ ቅዱስ «ክፉ ባልንጀርነት መልካሙን አመል ያጠፋል» በማለት ስለ መጥፎ ጓደኝነት ይነግረናል፥ 1ኛ ቆሮ. 15፡33። ልጆቻችሁ ቸሮችና ርኅሩሆች እንዲሆኑ ማስተማር አለባችሁ። በጸባያቸው ባለጌና ራስ ወዳዶች ከሆኑ ጓደኞች ጋር ቢገጥሙ እነርሱም እንደዚያ ዓይነት ጸባይ ሊኖራቸው እንደሚችል ልታስጠነቅቋቸው ይገባል። እንደ እናንተው መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነ መመሪያ ካላቸው ቤተሰቦችና ጓደኞች ጋር ጓደኝነት እንዲመሠርቱ ተስማሚ በሆነ መንገድ ምሩአቸው።

ለልጆቻችሁ የቸርነትና፥ የርኅራኄን ሥራ በተግባር እንዲገልጹ ለማስተማር አስቀድማችሁ እራሳችሁ በዚሁ የታነፃችሁ መሆን አለባችሁ። ወደ እራስ ወዳድነትና ወደ ዓመጸኝነት ከሚያመሩአቸው ጓደኞች ጋር እንዳይገጥሙ ጠብቁአቸው።



# ክፍል 3 - ትምህርት 13

## ኃላፊነት

ዓላማ፡- ወላጆች ልጆቻቸውን ኃላፊነት ወደሚወስዱበት ሁኔታ እንዲመሩአቸው ከዚያም ልጆቻቸው ኃላፊነት ለመሸከም የሚበቁ ዐዋቂዎች እንዲሆኑ አድርገው የሚያሳድጉበትን መንገድ መሠረት እንዲጥሉ ለመርዳት።

በቃል የሚጠና ጥቅስ፡- «ሰው በታናሽነቱ ቀንበር ቢሸከም መልካም ነው» ሰቆቃው ኤርምያስ 3፡27።

መግቢያ፡- ዮሴፍ ገና የአሥራ ሰባት ዓመት ልጅ በነበረ ጊዜ አባቱ ያዕቆብ ወደ እርሱ ጠራውና «ወንድሞችህ በሴኬም በጎችን የሚጠብቁ አይደሉምን? ወደ እነርሱ እልክህ ዘንድ ና» አለው።

ዮሴፍም «እነሆኝ» አለ።

ያዕቆብም በመቀጠል «ሄደህ ወንድሞችና በጎቹ ደኅና እንደሆኑ እይ፥ ወሬአቸውንም አምጣልኝ» አለው፥ ዘፍ. 37፡13-14።

ወንድሞቹ በጎቻቸውን ወደሚጠብቁበት ሥፍራ ወደ ሴኬም ለመድረስ ዮሴፍ ሰማኒያ ኪሎ ሜትር መጓዝ ነበረበት። ይህም መንገድ ቢያንስ ሁለት ቀናት ይወስዳል።

ሴኬም ከደረሰ በኋላ ወንድሞቹንና በጎቻቸውን ሊያገኛቸው አልቻለም። እነርሱን እየፈለገ ሳለ አንድ ሰው አገኘውና እነማንን እንደሚፈልግ ጠየቀው። ዮሴፍም ማንን እንደሚፈልግ ለሰውየው በነገረው ጊዜ ሰውየው «ከዚህ ሄደዋል፥ «ወደ ዶታን እንሂድ» ሲሉ ሰምቻቸዋለሁ!» ብሎ ነገረው።

ዮሴፍም ወንድሞቹን እስከሚያገኛቸው ድረስ በተጨማሪም ሰላሳ ኪሎ ሜትር ያህል ወደ ዶታን ተጓዘ። ዮሴፍም አድጎ እዚህ ዕድሜ እስኪደርስ ድረስ አባቱ ብዙ የሚሠሩት ሥራዎችን ሰጥቶት በሚገባ የሠራ መሆኑና ያዕቆብም አሁን ወንድሞቹን እንዲፈልግ በሚልከው ጊዜ ስራውን በሚገባ ይሰራል ብሎ የተማመነበት መሆኑ አያጠራጥርም።

### ገና በልጅነታቸው ኃላፊነትን ማስተማር ጀምሩ።

በዚህች ትንሽ መጽሐፍ ውስጥ በመደጋገም «ገና በልጅነታቸው ጀምሩ» በማለት ተናግረናል። ከመደጋገሙ የተነሣ ለመስማት ትሰለቹ ይሆናል! ነገር ግን አሁንም ቢሆን እውነት ነው። ልጆቻችሁ ገና ሕፃን ሳለ በየቀኑ የሚሠራውን ቀላል የሆነ «ሥራ» ስጡት። በየቀኑ የሚሠራ መሆኑን ተቆጣጠሩ። በምትፈልጉበት ጊዜ ሌሎች ሥራዎችንም ሊሠራላችሁ ይችላል! ነገር ግን ያንን የተሰጠውን ሥራ በየቀኑ የሚሠራ መሆኑን ተቆጣጠሩ። በአንድ ምክንያት ሥራውን ትቶ መሄድ ቢያስፈልገው፥ ሌላ ሰው እንዲሠራለት መጠየቅ አለበት! ምክንያቱም ያንን ሥራ መንከባከብ የራሱ ኃላፊነት ነው።

ትንሽ አደግ በሚልበት ጊዜ እንደ ችሎታውና እንደ ዕድሜው ሌሎች «ኃልፊነቶችን» ጨምሩለት። ለምሳሌ ወንድ ልጃችሁን የማገዶ እንጨት የመፍለጡና ከአንድ ቦታ የመቆለሉን ኃላፊነት ልትሰጡት ትችላላችሁ። አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ደግሞ ምግብ የማብሰያውን ከሰል አዘጋጅቶ የማስቀመጡን ኃላፊነት ልትሰጡት ትችላላችሁ። አጥር ገቢውን ሊያጸዳና

ቆሻሻዎቹንም ለቅሞ ሊያቃጥል ይችላል። በረንዳውን ሊጠርግ ይችላል። በየቀኑ ምን ዓይነት ሥራ መሥራት እንዳለበት ታውቃላችሁ። ወተት ማምጣት የእርሱ ሥራ ሊሆን ይችላል። ወንዶች ልጆች እያደጉ በሚሄዱበት ጊዜ ጸባያቸውን ለማስተካከልና ያላቸውንም ትርፍ ጉልበት ሊጠቀሙበት እንዲችሉ ኃይለኛ ሥራ መሥራት ያስፈልጋቸዋል።

ሥራ ፈት የሆነች ልጅ አታሳድጉ! በመጠኑም ቢሆን በየቀኑ ጠረጴዛ ማጽዳትን፥ ምግብ ከተበላ በኋላ ሰሃን ማጠብን፥ አልጋ ማንጠፍን፥ ቤት መወልወልንና ምግብ ማዘጋጀትን ልትማር ትችላለች። ልክ እንደ ወንድሟ ሁልጊዜ ቅዳሜ ጠዋትና ከት/ቤት በኋላ አብራችሁ ልትሠራ ትችላለች።

መልካም ጠባይ መመሥረት የሚቻለው ተራ በተራ በማስተማር ነው። አንዱን መልካም ጸባይ ካስተማሩ በኋላ ሌላውን በሌላ ጊዜ ማስተማር ይቻላል። የሆነውን ትምህርት ሁሉ በአንድ ጊዜ ልጆቻችን ይማራሉ ብላችሁ አትጠብቁ። ቀስ በቀስ የሚያድገውን መልካም የሆነ ጸባይ ለማስገኘት በተስፋ ሥሩ።

አንድ ቤተሰብ ስለ ልጆቻቸው አስተዳደግ በሚገዳቸው ወላጆች እንክብካቤና ፍቅር ሥር ሲያድግና ሲገነባ ማየት በጣም ደስ ያሰኛል። አበባዎች በጸሐይ ሙቀት እየፈኩ ራሳቸውን ወደ ላይ እንደሚያቀኑ ልጆቻችሁም በጸሎትና በዓላማችሁ ጸንታችሁ ሥነ ሥርዓትን ብታስተምሩአቸውና መሄድ ባለባቸው መንገድ እንዲሄዱ ብትመሩአቸው እነርሱም እየፈኩና በመንፈስ እየጸኑ ያድጋሉ።

ልጆቻችሁ በዕድሜያችሁ ከ12-14 ባለው ክልል ውስጥ በሚገቡበት ጊዜ የተወሰኑ ሥራዎች ሳይነገሩ አስበው እናንተም በጥብቅ ሳትቆጣጠሩአቸው መሥራት አለባቸው። መደበኛ የሆነ ኃላፊነትን በመውሰድ በኩል ይበልጥ ብስለትን እያገኙ ሲሄዱ እናንተም ይበልጥ ነፃነትን ልትሰጡአቸው ትችላላችሁ። ግደግ ያለባቸው ኃላፊነትን በመቀበል ብቻ አይደለም! በአካል፥ በማኀበራዊ ኑሮ፥ በስሜትና በዕውቀትም ማደግ አለባቸው። በነዚህ መስኮች ሁሉ እንዲያድጉ እናንተ እንድትረዱአቸው ያስፈልጋል።

«የተባረከ ቤተሰብ» በሚል ርዕስ ከሚወጡት ተከታታይ መጻሕፍት የመጨረሻው «በተለይ ለወጣቶች» የሚለው ይሆናል! ይህም መጽሐፍ ለወላጆችና ለወጣቶች የአንድ ሰው ጸባይ በሚታነጽበት ከ13-20 ባለው የዕድሜ ክልል ውስጥ ጌታን እያስደሰቱ መኖር ስለሚቻልባቸው መንገዶች አዳዲስ አሳቦችን ይሰጣል።

ልጆቻችሁን ለጌታ ክብር እንዲሆኑ በምታሳድጓቸው ጊዜ ሁሉ እግዚአብሔር ይባርካችሁ። አሜን።

